Initiative Africa

ም
ም ረ ጥ
ጬ
2013

# የመራጮች ትምህርት ማስተማሪያ ማንዋል



IA/IRI-DOC/MNL/21/002

መጋቢት፥ 2013

© ኢኒሽየቲቭ አፍሪካ
2013 ዓ.ም

ም
ም ረ ጥ
ጫ

2013

## ማውጫ


| **መግቢያ** | **ገጽ** |
| --- | --- |
| የማንዋሉ ዓላማ | ii |
| የማንዋሉ ተጠቃሚዎች | ii |
| የተሳታፊዎች ትውውቅ | ii |
| | |
| **1. ዴሞከራሲ እና ዴሞከራሲያዊ ስርዓት** | **1** |
| 1.1. ዴሞክራሲ እና ሕገ መንግስታዊ ዴሞክራሲ | 1 |
| | |
| **2. የሕዝብ ውክልና ተቋማት በኢትዮጵያ** | **2** |
| 2.1. የኢትዮጵያ ሥርዓተ መንግስትና የመንግስት አወቃቀር | 2 |
| 2.2 . የፌደራሉ መንግስት የሕዝብ ውክልና ተቋማት | |
| | |
| **3. የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ አወቃቀር ስልጠናና ተግባር** | **4** |
| 3.1. የኢትዮጵያ የምርጫ ቦርድ አወቃቀር | 7 |
| 3.2. የቦርዱ የክልል ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት | 8 |
| 3.3. የምርጫ ክልሎች | 9 |
| 3.4. የምርጫ ጣቢያዎች | 10 |
| 3.5. የምርጫ አስፈጻሚዎች ተግባርና ኃላፊነቶች | 10 |
| | |
| **4. የምርጫ ሕግጋትና እና የምርጫ ሒደቶች በኢትዮጵያ** | **13** |
| 4.1. የኢትዮጵያ የምርጫ ስርዓትና የሚካሄዱ የምርጫ ዓይነቶች | 13 |
| 4.2. ምርጫ እና ዴሞከራሲ | 14 |
| 4.3. ለመራጮች ስለሚሰጡ የምርጫ መረጃዎች | 14 |
| 4.4. የመራጮች ምዝገባ | 15 |
| 4.5. የእጩዎች ምዝገባ | 16 |
| 4.6. ስለ ምርጫ ዘመቻ | 17 |
| 4.7. ስለ ድምፅ አሰጣጥ | 17 |
| 4.8. የድምጽ ቆጠራና ውጤት አገላለጽ | 19 |
| | |
| **5. በዴሞክራሲያዊ ምርጫ የዜጎች መብቶችና ኃላፊነቶች** | **22** |
| 5.1. በዴሞክራሲያዊ ምርጫ የዜጎች መብቶች | 22 |
| 5.2. በዴሞክራሲያዊ ምርጫ የዜጎች ከመምረጥ መመረጥ ባሻገር | 23 |
| 5.3. በዴሞክራሲያዊ ምርጫ የሴቶች ተሳትፎ | 24 |
| 5.4. በዴሞክራሲያዊ ምርጫ የአካል ጉዳተኞች፣የተፈናቃዮች፣አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ሰዎች ተሳትፎ | 24 |
| | |
| **6. በምርጫ ሒደት የሚነሣ አቤቱታ እና ክርክር የሚፈታበት ተቋም እና የሚስተናገዱበት ሥርዓት** | **26** |
| 6.1. በምርጫ ወቅት የሚከሰቱ ቅሬታዎች እና አለመግባባቶች | 26 |
| 6.2. በምርጫ ሂደት የሚከሰቱ ቅሬታዎች እና አቤቱታዎች መፍቻ ሥርዓት እና ተቋማት | 27 |
| | |

## መግቢያ

ኢኒሽየቲብ አፍሪካ ባልፉት ጊዜያት የሥነ ዜጋና የመራጮች ትምህርትና ስልጠና በተለይ ለመጀመሪያ ጊዜ መራጮች ሲሰጥ ቆይቷል። ይህንን ተግባር ለመወጣት እንዲያስችለው የሥነ ዜጋ ትምህርትና ስልጠና ሰነዶች እያዘጋጀ ሲሰራ ቆይቷል። ይህ የማስተማሪያ መጽሐፍም በ2003 ዓ.ም እና በ2012 ዓ.ም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የተዘጋጁትን ማኑዋሎች መሰረት በማድረግና ኢኒሽየቲብ አፍሪካ ሲጠቀምባቸው የነበሩትን ማንዋሎች በማሻሻል በ ተዘጋጅቶ የቀረበ ነው።

የመራጮች ትምህርት የሚከተሉት ግቦች አሉት፤

1) የምርጫ ሕግጋቱን ምንነት መረዳትና ሕግጋቱም ነጻ፣ ገለልተኛ እና ተዓማኒ ምርጫ ማከናወን ያስችላሉ የሚል እምነት እንዲይዙ ማድረግ፣

2) የምርጫ አስፈጻሚ አካላትን ተግባርና ኃላፊነት ማወቅና ተቋማቱ ነጻ፣ ገለልተኛና ተዓማኒ ምርጫን ለማካሄድ ብቃት ያላቸው መሆኑን እንዲያምኑ ማድረግ፣

3) በምርጫ ወቅት የሚነሱ ግጭቶች/አለመግባባቶች የሚፈቱበት የዳኝነት አካላትና ስርዓቶች መኖራቸውንና አሰራራቸውን ማሳወቅ፣

4) ዜጎች በመራጭነታቸው የሚወጧቸው ኃላፊነቶች መኖራቸውን እንዲረዱ ማስቻል። ይህ የማስተማሪያ መጽሐፍ ከላይ የተመለከቱትን የሥነ ዜጋና የመራጮች ትምህርት ግቦች ሊያሳኩ የሚችሉ ይዘቶች ተካተውበት የተዘጋጀ ነው።

**የማንዋሉ ዓላማ**

የዚህ መጽሐፍ አላማ ሰልጣኞች (መራጩ ህዝብና የምርጫ አስፈጻሚዎች) ሥነ ዜጋዊ ዕውቀት፣ ክህሎትና ባህሪያት እንዲያዳብሩ እንዲሁም ስለ ዴሞክራሲያዊ ምርጫና የዜጎች ተሳትፎ ዕውቀት እንዲኖራቸው ማስቻል ነው። መጽሐፉ ለሰልጣኞች ስለ ምርጫና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እውቀትና መረጃ ማስጨበጥ ብቻ ሳይሆን ለዴሞክራሲያዊ አሰራርና ስኬት አዎንታዊ አመለካከት በዜጎች ዘንድ እንዲፈጠር ማድረግ ነው።

## የማንዋሉ ተጠቃሚዎች

የዚህ መጽሐፍ ተጠቃሚዎች የመራጮች ትምህርት ለመስጠት የሚዘጋጁ ሰልጣኞች ናቸው።

## የስልጠናው አጀማመር

የፕሮግራሙ አስተባባሪዎች እራሳቸውን አስተዋውቀው የስልጠናውን ዓላማ በሚመለከተው ተወካይ በኩል እንዲተላለፍ ይደረግ። ወቅቱ የኮቪድ ወቅት እንደመሆኑ አስፈላጊው የጥንቃቄ ሁኔታ መሟላቱን ማረጋገጥ ተገቢ ነው። ተሳታፊዎች ማድረግ ስላለባቸውና ስሌለባቸው ነገሮች ማስገንዘብ ይገባል።

## የተሳታፊዎች ትውውቅ

የፕሮግራሙ አስተባባሪዎች አሰልጣኞችና ሰልጣኞች በየተራ ራሳቸውን እንዲያስተዋውቁ ማድረግ አለባቸው። በዚህ ወቅት የሚከተሉት እንዲነሱ መጠየቅ ይገባል።

- ✓ ስም
- ✓ የስራና የትምህርት ሁኔታ
- ✓ ባለፉት ምርጫዎች የነበራቸው ተሳትፎ
- ✓ ከዚህ ስልጠና የሚጠብቁት አንድ ውጤት

## የማነቃቂያ ተግባር

**አሰልጣኝ፡-** ተሳታፊዎችን በክብ ያስቁሟቸውና የሚከተለውን ትዕዛዞች ይስጧቸው።

1) ‹ምርጫ› የሚለውን ቃል ስትሰሙ ወደ አዕምሯችሁ የሚመጣውን ቃል ወይም ዐረፍተ ነገር ከጎን ላለው ሰው ይንገሩ።
2) እያንዳንዱ ተሳታፊ የተነገረውን ቃል ወይም ዐረፍተ ነገር ከነገረው ሰው ስም ጋር ለሌሎች ይናገር ።



## ምዕራፍ 1. ዴሞክራሲ እና ሕገ መንግስታዊ ዴሞክራሲ

ሰልጣኞች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፤

- የዴሞክራሲን ምንነት ይረዳሉ፣
- በኢትዮጵያ <የውክልና ዴሞክራሲ> ማሳያዎችን ይዘረዝራሉ።

### ተግባር 1፡- አጠቃላይ ውይይት

**አሰልጣኝ፡-** የሚከተሉት ጥያቄዎችን ለተሳታፊዎች በማቅረብ የመነሻ ውይይት ያካሂዱ።

3) ‹ዴሞክራሲ› ማለት ምን ማለት ነው?
4) ‹ዴሞክራሲ› የሚለውን ቃል ስትሰሙ ወደ አዕምሯችሁ የሚመጣው ምንድን ነው?
5) <የውክልና ዴሞክራሲ> ማለት ምን ማለት ነው?
6) በኢትዮጵያ <የውክልና ዴሞክራሲ> ለመኖሩ ማሳያው ምንድን ነው?

**አሰልጣኝ፡-** የሚከተለው ጽሁፍ ላይ ያሉ ሃሳቦችን በማንጸባረቅ ውይይቱን ይደምድሙ።

‹ዴሞክራሲ› የሚለው ቃል የኢንግሊዝኛ ቃል ሲሆን ቀጥተኛ ምንጩ የፈረንሳይኛ ቃል የሆነው 'démocratie' ነው፤ የእንግሊዝኛ ቋንቋ አካል የሆነው ከ16ኛው መ/ክ/ዘመን ጀምሮ ሲሆን ቀደምት ምንጩ "ዴሞክራሽያ" (demokratia) የሚለው የግሪክ ቃል ነው። demokratia፡ demos እና kratos ከተሰኙ ሁለት የግሪክ ቃላት ቅንጅት የመጣ ቃል ነው፤ ትርጉማቸውም demos ህዝብ ማለት ሲሆን kratos ደግም አስተዳደር ወይም መሪነት (rule) ነው። ስለዚህ በዚህ ቀጥተኛና ጥንታዊ ትርጉሙ ዴሞክራሲ ማለት *የህዝብ ራስን በራስ ማስተዳደር ማለት ነው።*

የውክልና ዴሞክራሲ መገለጫዎች ሁሉም ዕድሜያቸው የደረሰ የሕብረተሰብ ክፍሎች የሚሳተፉበት ምርጫ መካሄድ፤ የምርጫው በተወሰነ ጊዜ ያለ ማቋረጥ መካሄድ፣ ምርጫው ነጻ፣ ገለልተኛና ተዓማኒ መሆን፣ የመናገር፣ የመሰብሰብ የመደራጀትና ሌሎች የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበርና ተዘማጅነት ያላቸው ተቋማት መኖር ናቸው። እነዚህ መብቶች በተሟሉበት የፖለቲካ ምሕዳር ዜጎች በነጻነት በመረጧቸው ወኪሎች የሚተዳደሩበት ስርዓት ነው።

የውክልና ዴሞክራሲ መሰረታዊ ትርጉም ህዝብ ወይም መራጩ ህዝብ በመረጣቸው ወኪሎቹ አማካኝነት የሚተዳደርበት፣ ውሳኔ የሚወስንበት ሥርዓት ነው። ይህም ስርዓት በሰፊው (ተለጥጦ) ሲተረጎም ህዝብ እስከወሰነ ድረስ የውሳኔዎቹ ይዘት ምንም ይሁን ምን ማናቸውም ጉዳዮች በህዝብ በዴሞክራሲያዊ መንገድ ተወስነው ሊፈጸሙ ይችላሉ የሚል ድምዳሜ ላይ ሊያደርሰን ይችላል። ይሄውም ለምሳሌ ህዝብ እስከወሰነ ድረስ የግለሰቦች መብት ሊጣሱ ይችላሉ ወደሚል መደምደሚያ ያደርሳል። ነገር ግን እነዲህ አይነት ችግሮች እዳይከሰቱ ዴሞክራሲ በትክክል በስራ ላይ በሚውልባቸው አገራት የዴሞክራሲ ትግበራ ከሕገ መንግስታዊነት እና ከሕግ የበላይነት ጋር ተቀናጅቶና ተዳምሮ ነው የሚፈጸመው። ይህም ስርዓት ሕገመንግስታዊ ዴሞክራሴ (constitutional democracy) በመባል ይታወቃል። በሕገ መንግስታዊ ዴሞክራሲ ስርዓት በህዝብ የተመረጠ መንግስት ስልጣን በሕገ መንግስት የተገደበ የሚሆንበት ስርዓት ነው። በሌላ አነጋገር ሕገ መንግስቱ በህዝብ የተመረጠ መንግስትን ስልጣንና ኃላፊነቶች እንዲሁም የመንግስትን የስልጣን ገደብም ይደነግጋል።



## ምዕራፍ 2. የሕዝብ ውክልና ተቋማት በኢትዮጵያ

ሰልጣኞች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፤

- ኢትዮጵያ የምትከተለውን ስርዓተ መንግስትና የመንግስት አወቃቀር ይረዳሉ፣
- የኢትዮጵያን የፌዴራል ሥርዓት ዋና ዋና መገለጫዎችን ይዘረዝራሉ፣
- በፌዴራሉ መንግስት ደረጃም ሆነ በክልሎች ያሉትን የህዝብ ውክልና ተቋማት ምንነትና ስልጣን እና ተግባሮቻቸውን ያውቃሉ።

### ተግባር 2.1፡- የቡድን ውይይት

**አሰልጣኝ፡-** ሰልጣኞችን በአምስት በአምስት በማድረግ ቡድኖች እንዲቋቋሙ ያድርጉ። የሚከተለውን ጥያቄ ላይ በየቡድናቸው ውይይት ያካሂዱ።

- ኢትዮጵያ የምትከተለው ሥርዓተ መንግስት ፓርላሜንታዊ እንደመሆኑ ዋና ዋና መገለጫዎቹ ምንድን ናቸው?

**አሰልጣኝ፡-** እያንዳንዱ ቡድን የተወያየባቸውን ነጥቦች ለተሳታፊዎች በማቅረብ አጠቃላይ ውይይት ያካሂዱ። በመጨረሻም የሚከተለው ጽሁፍ ላይ ያሉ ሃሳቦችን በማንጸባረቅ ውይይቱን ይደምድሙ።

### 2.1. የኢትዮጵያ ሥርዓተ መንግስትና የመንግስት አወቃቀር

ኢትዮጵያ ፓርላሜንታዊ ስርዓተ መንግስት ተከታይ እንደሆነች ሕገ መንግስቱ በአንቀጽ 45 ስር በግልጽ አስቀምጧል። የኢትዮጵያ የመንግስት አወቃቀርም ፌደራላዊ እንደሆነ በሕገ መንግስቱ በግልጽ ተመልክቷል፤ ክልሎችም ተቋቁመዋል፤ የስልጣን ክፍፍልም በሁለቱ የመንግስት እርከኖች መካከል ተደርጓል።

የኢትዮጵያ ሥርዓተ መንግስት ፓርላሜንታዊ ነው ስንል ዋና ዋና መገለጫዎቹ የሚከተሉት ናቸው፤

- በቀጥታ በሕዝብ የሚመረጠው የሕግ አውጪው ማለትም የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ነው።
- ዋና የሕግ አስፈጻሚው (ጠቅላይ ሚኒስትሩ) ለዚህ ስራ በቀጥታ በህዝብ አይመረጥም፣ ይልቁንም ዋና የሕግ አስፈጻሚው የሕግ አውጪው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባልና የሚሰየመውም በዚሁ ም/ቤት ነው።
- ጠቅላይ ሚኒስትሩን ጨምሮ ጠቅላላ የካቢኔ (የሚንስትሮች ም/ቤት) አባላት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት ሊሆኑ ይችላሉ። ስለሆነም በሕግ አውጪውና በሕግ አስፈጻሚው አካላት መካከል የጠራ ክፍፍል የለም።
- ጠቅላይ ሚኒስትሩና ካቢኔው በስልጣን ላይ መቆየት የሚችሉት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የአብላጫ ወንበር ባለቤት በሆነው ፓርቲ ወይም የፓርቲዎች ጥምረት ይሁንታና ድጋፍ እስካለው ድረስ ብቻ ነው። ስለሆነም የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በጠ/ሚኒስትሩና በሚንስትሮች ም/ቤት ላይ የፖለቲካ የስልጣን የበላይነት አለው፡ ፡ ይህም ሁኔታ በሕገ ምንግስቱ ውስጥ በግልጽ ተመልክቷል፤ አንቀጽ 50 (3)፡ ‹የፌደራሉ መንግስት ከፍተኛ የስልጣን አካል የፌደራሉ መንግስት የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ነው፣ ተጠሪነቱም ለአገሪቱ ህዝብ ነው›። አንቀጽ 72(2)፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩና የሚንስትሮች ም/ቤት ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ተጠሪዎች ናቸው›።

ከላይ ስለ ኢትዮጵያ ፌደራል መንግስት ፓርላሜንታዊ መገለጫዎች ያነሳናቸው ነጥቦች ክልሎችንም ሆነ የአዲስ አበባንና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችንም ይመለከታሉ። የክልል ርዕሰ መስተዳድሮች የክልል ም/ቤቶች አባላት ናቸው፤ ተጠሪነታቸው ለክልሉ ም/ቤቶች ነው። የክልል ከፍተኛ የስልጣን አካል የክልሉ ም/ቤት ነው፣ ተጠሪነቱም ለወከለው ክልል ህዝብ ነው (በህገ መንግስቱ አንቀጽ 50(3) ስር እንደተደነገገው)። የክልል መስተዳደር ም/ቤት (ርዕሰ መስተዳድሩና ካቢኔው) በስልጣን መቆየት የሚችሉት በክልል ም/ቤት አብላጫ መቀመጫ ያለው ፓርቲ ወይም የፓርቲዎች ጥምረት እስከደገፈው ድረስ ብቻ ነው።

### ተግባር 2.2፡- የቡድን ውይይት

**አሰልጣኝ፡-** ሰልጣኞችን በሁለት ቡድኖች እንዲከፈሉ ያድርጉ። አንደኛው ቡድን በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሌላኛው ደግሞ በፌዴሬሽን ምክር ቤት በአባላት አመራረጥ እንዲሁም በየምክር ቤቶቹ ሃላፊነትና ተግባራት ላይ ይወያዩ።

**አሰልጣኝ፡-** ቡድኖቹ የተወያዩባቸውን ነጥቦች በተወካዮቻቸው ለተሳታፊዎች በማቅረብ አጠቃላይ ውይይት ያካሂዱ። በመጨረሻም የሚከተለው ጽሁፍ ላይ ያሉ ሃሳቦችን በማንጸባረቅ ውይይቱን ያጥናቁ።

## 2.2. የፌደራሉ መንግስት የሕዝብ ውክልና ተቋማት

በፌዴራሉ መንግስት ደረጃ ህዝብ የሚወከልባቸው ሁለት ምክር ቤቶች አሉ። እነሱም የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና የፌዴሬሽን ምክር ቤት ናቸው። ነገር ግን ለፌዴራሉ መንግስት ተጠሪ የሆኑት ሁለት የከተማ አስተዳደሮችም (አዲስ አበባ እና ድሬዳዋ) የየራሳቸው የከተማ ምክር ቤት ያላቸው ሲሆን በአዲስ አበባ በተጨማሪ የክፍለ ከተማ ምክር ቤትና የቀበሌ ምክር ቤቶች ሲኖሩ በድሬዳዋ ደግሞ የቀበሌ ምክር ቤቶች አሉ።

### የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፡

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት ሁሉ አቀፍ፣ ነጻ፣ ቀጥተኛ፣ ትክክለኛ በሆነና ድምጽ በሚስጥር በሚሰጥበት ሥርዓት በየ5ት ዓመቱ በህዝብ ይመረጣሉ። የምክር ቤቱ ጠቅላላ አባላት ከ550 መብለጥ የለበትም። እስካሁን በተደረጉት ምርጫዎች የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት 547 ነበሩ። ይህ ማለት አገሪቱ በ547 የምርጫ ክልሎች ተከፋፍላ በእያንዳንዱ የምርጫ ክልል ከሚቀርቡት ተወዳዳሪዎች መካከል አንድ ተመራጭ ብቻ የሚመረጥበት ሥርዓት ነው ማለት ነው።

የምክር ቤቱ አባላት የሚመረጡት በሁለት መንገድ ነው፤

1) ከሃያ የማያንሱ የተለየ ውክልና ያስፈልጋቸዋል ተብሎ የታመነባቸው አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች በሚወከሉበት የተለየ የምርጫ ሥርዓት፣
2) የተቀሩት የምክር ቤቱ አባላት የሚመረጡት በአንድ የምርጫ ክልል ውስጥ ከሌሎች ተወዳዳሪዎች መካከል አብላጫ ድምጽ ያገኘ ተወዳዳሪ አሸናፊ በሚሆንበት የምርጫ ሥርዓት ነው።

የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት የመላው የአገሪቱ ህዝብ ተወካዮች ናቸው። ተወካዮቹ ተገዢነታቸው፣

- ለሕገ መንግስቱ
- ለህዝቡ፣ እና
- ለህሊናቸው ብቻ እንደሆነ ሕገ መንግስቱ በማያሻማ መንገድ አስቀምጦታል።

የምክር ቤቱ አባላት ዋና ስራቸው የሆነውን የሕዝብ እንደራሴነት ተግባራቸውን ያለምንም ፍርሃትና መሸማቀቅ እንዲያከናውኑ ሲባል በምክር ቤቱ ውስጥ በሚሰጡት ድምጽ ወይም አስተያየት ምክንያት አይከሰሱም፤ አስተዳደራዊ እርምጃም አይወሰድባቸውም። እንዲሁም አንድ የምክር ቤት አባል ከባድ ወንጀል ሲፈጽም እጅ ከፍንጅ ካልተያዘ በስተቀር ያለ ምክር ቤቱ ፈቃድ አይያዝም፣ በወንጀልም አይከሰስም።

የተመረጠበት የምርጫ ዘመን ሳይጠናቀቅ አንድ የም/ቤቱ አባል የመረጠው ህዝብ ዓመኔታ ካጣበት ከአባልነቱ ሊነሳ እንደሚችል ሕገ መንግስቱ ይደነግጋል። ይህ የማስነሳት ሥርዓት የሚፈጸምበት የሕግ ማዕቀፍ በአዋጅ ቁጥር 88/1989 ተቀምጧል። ይህ አዋጅ መራጮች የመረጡትን ተወካይ የመገምገም፣ የመተቸትና የመመርመር መብት እንዳላቸው ይደነግጋል።

የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ዋነኛው የፌዴራሉ መንግስት ቀጥታ የህዝብ ውክልና ያለው ተቋም ስለሆነ ሕግን ከማውጣት በተጨማሪ በርካታ ሌሎች ስልጣንና ተግባራትም አሉት። እነዚህም በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 55 ስር ተዘርዝረዋል።

በዚሁ መሠረት የምክር ቤቱ ስልጣንና ተግባራት ሕግ የማውጣት፣ ተቋማትን የማቋቋም/የማደራጀት፣ የአስፈጻሚውን አካል መቆጣጠር፣ አገር አቀፍ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎችን ማጽደቅ፣ የአገሪቱን ሰላምና ደህንነት ማስጠበቅ፣ የዳኞችንና የሌሎች ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊዎች ሹመቶችን መስጠት/ ማጽደቅ እና መሰል ስልጣንና ኃላፊነት በሕገ መንግስቱ ተሰጥቶታል። ሕገ መንግስቱ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከሰጣቸው ስልጣንና ተግባራት ውስጥ የሚከተሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

1. <u>በሕግ ማውጣት ረገድ</u>፣ በማናቸውም የፌደራሉ መንግስት የስልጣን ክልል ውስጥ ባሉ ጉዳዮች ላይ ሕግ የማውጣት ስልጣኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ዝርዝር ሕግ እንደሚያወጣ አንቀጽ 55 ይደነግጋል፤
   ሀ) መሬትና ተፈጥሮ ሀብት እንዲሁም ድንበር ተሻጋሪ ወይም ከአንድ ክልል በላይ የሚያስተሳስሩ ወንዞችና ሐይቆች አጠቃቀም፣
   ለ) በክልሎች መካከል የሚኖረውን የንግድ ልውውጥ፣እንዲሁም የውጭ ንግድ ግንኙነት በሚመለከት፣
   ሐ) የአየር የባቡርና የባሕር መጓጓዣ፣ የፖስታና ቴሌኮምዩኒኬሽን አገልግሎቶችን እንዲሁም ሁለት ወይም ከሁለት በላይ ክልሎችን የሚያገናኙ አውራ መንገዶችን በተመለከተ፣
   መ) በዚህ ሕገ መንግስት የተደነገጉትን የፖለቲካ መብቶች አፈጻጸምን እንዲሁም ምርጫን በተመለከተ፣
   ሠ) የዜግነት መብትን፣ የኢሚግሬሽን፣ የፓስፖርትን፣ ወደ አገር መግቢያና መውጫ ጉዳዮችን እንዲሁም የስደተኞችና የፖለቲካ ጥገኝነት ጉዳዮችን በተመለከተ፣
   ረ) አንድ ወጥ የመጠን መለኪያ ደረጃና የጊዜ ቀመር፤ የፈጠራና የስነ ጥበብ መብቶችን በተመለከተ እና የጦር መሳሪያ መያዝን የሚመለከት፣
   ሰ) የሰራተኞች ጉዳይ ሕግ፣ የንግድ ሕግ፣ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ፣
   ሸ) አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብን ለመፍጠር ሲባል በፌዴራል መንግስት ሕግ እንዲወጣላቸው የሚያስገድዱ ለመሆናቸው በፌዴሬሽኑ ምክር ቤት የታመነባቸው የፍትሐብሔር ሕጎችን
   ቀ) ገንዘብን፣ የብሔራዊ ባንክን አስተዳደር፣ የውጭ ምንዛሪንና ልውውጥን በተመለከተ ዝርዝር ሕግ

2. <u>ከሕግ ማውጣት ውጪ</u> ካሉት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባራት መካከልም ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፤
   ሀ) የፌደራል መንግስት፣ የአገርና የህዝብ መከላከያ፣ የደህንነትና የፖሊስ ኃይል አደረጃጀት ይወስናል
   ለ) በሕገ መንግስቱ በተመለከተው መሰረት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ያውጃል፣ የሕግ አስፈጻሚው የሚያወጣውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ተመልክቶ ይወስናል፣
   ሐ) የሚኒስትሮች ም/ቤት በሚያቀርበው የሕግ ረቂቅ መሰረት የጦርነት አዋጅ ያውጃል፣
   መ) የአገሪቱን አጠቃላይ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊ፣ የልማት ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን የፋይናንስና የገንዘብ ፖሊሲን ያጸድቃል፣
   ሠ) ለፌደራል መንግስት በተከለለው የገቢ ምንጭ ክልል ግብርና ታክስ ይጥላል፣ የፌደራል መንግስት በጀት ያጸድቃል፣
   ረ) የሕግ አስፈጻሚው አካል የሚዋዋላቸውን አለም አቀፍ ስምምነቶች ያጸድቃል።
   ሰ) የፌደራል መንግስት ፍርድ ቤት ዳኞችን፣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት አባላትን፣ የኮሚሽነሮችን፣ የዋናው ኦዲተርን እንዲሁም የሌሎች ሹመታቸው በም/ቤቱ መጽደቅ ያለበትን ባለስልጣኖች ሹመት ያጸድቃል፣
   ሸ) የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽንና የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋምን ያቋቁማል፣ ስልጣንና ኃላፊነታቸውን ይወስናል፣
   ቀ) በማንኛውም ክልል ሰብዓዊ መብቶች ሲጣሱና ክልሉ ድርጊቱን ማቆም ሳይችል ሲቀር፣ በራሱ አነሳሽነትና ያለክልሉ ፈቃድ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ለፌደሬሽኑ ም/ቤትና ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት የጋራ ስብሰባ ጥያቄ ያቀርባል፣ በተደረሰበት ስምምነት መሰረት ለክልሉ መመሪያ ይሰጣል፣

በ) ም/ቤቱ ጠቅላይ ሚ/ሩን እና ሌሎች የፌደራሉ መንግስት ባለስልጣናትን ለጥያቄ የመጥራትና የሕግ አስፈጻሚውን አካል አሰራር የመመርመር ሥልጣን አለው፣

ተ) ለሕግ አስፈጻሚው አካል በተሰጠ ማንኛውም ሥልጣን ላይ የምክር ቤቱ አባላት በ1/3ኛ ድምጽ ሲጠይቁ ምክር ቤቱ ይወያያል፣ ምክር ቤቱ በጉዳዩ ላይ የመመካከርና አስፈላጊ መስሎ የታየውን እርምጃ የመውሰድ ሥልጣን አለው፣

ቸ) ምክር ቤቱን የሚመሩ አፈ ጉባኤና ም/አፈ ጉባኤ ይመርጣል፣ አስፈላጊ ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴዎችን ያዋቅራል፡፡

የፌደራሉን መንግስት የሕግ አስፈጻሚ አካል የሚመሰርተውና የሚመራው በህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ውስጥ አብላጫ መቀመጫ ያገኘ (ማለትም 50% ሲደመር አንድ መቀመጫ ያገኘ) የፖለቲካ ድርጅት ወይም ጣምራ ድርጅት ነው፡፡ ስለዚህ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት የፌደራሉ መንግስት የሕግ አስፈጻሚ አካልም ምንጭ ነው ማለት ነው፡፡

የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ከአባላቱ ከግማሽ በላይ ከተገኙ የየእለት ስራውን ለማከናወን ምልዓተ ጉባኤ ይኖረዋል፡ ፡ በሕገ መንግስቱ ውስጥ ወይም በሌሎች ሕጎችም በግልጽ ከተደነገገባቸው ጉዳዮች በስተቀር ማንኛውም የምክር ቤቱ ውሳኔዎች የሚተላለፉት በም/ቤቱ አባላት የአብላጫ ድምጽ ነው፡፡ አመታዊ የስራ ጊዜውም (በመካከሉ የአንድ ወር እረፍት የሚወስድ ሆኖ) ከመስከረም ወር የመጨረሻ ሰኞ እስከ ሰኔ 30 ድረስ ነው፡፡ ምክር ቤቱ የሚመረጠው ለ5 ዓመት የስራ ዘመን ነው፤ ቀጣይ ምርጫም ተካሂዶ መጠናቀቅ ያለበት በሰራ ላይ ያለው ምክር ቤት ስራ ዘመን ከመጠናቀቁ አንድ ወር በፊት ነው፡፡ ነገር ግን ምክር ቤቱ የስራ ዘመኑን ሳይጨርስ እንዲበተን የሚያስገድዱ ሁኔታዎች ከተፈጠሩ ም/ቤቱ ተበትኖ አዲስ ምርጫ የሚደረግበት ሁኔታ ሊከሰት ይችላል፡፡

## የፌደሬሽን ምክር ቤት፡

የፌደሬሽን ምክር ቤት ሁለተኛው የፌደራሉ መንግስት ም/ቤት ነው፡፡ ይህ ም/ቤት በሕገ መንግስት ማሻሻያ ሂደት ከሚያደርገው ተሳትፎ በስተቀር ቀጥተኛ የሕግ ማውጣት ስልጣን የለውም፡፡ የፌደሬሽን ም/ቤት በፌደራሉ መንግስት አባል ክልሎች የሚገኙት ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች የሚወክሏቸው አባላት የሚወከሉበት ም/ቤት ነው፡፡ አወካከሉንም በተመለከተ የሕገ መንግስቱ አንቀጽ 61 እንደሚደነግገው፡ እያንዳንዱ ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝብ ቢያንስ አንድ ተወካይ ይኖረዋል፣ በተጨማሪም የብሔር ወይም ብሔረሰቡ አንድ ሚሊዮን ህዝብ አንድ ተጨማሪ ወኪል ይኖረዋል፡፡ የፌደሬሽን ም/ቤት አባላትን አመራረጥ በተመለከተ አባላቱ በክልል ም/ቤቶች እንደሚመረጡ ሕገ መንግስቱ ያስቀምጣል፡፡ የክልል ም/ቤቶች ወይ እራሳቸው አባላቱን ይመርጣሉ ወይ ደግሞ አባላቱ በቀጥታ በሕዝብ እንዲመረጡ ማድረግ ይችላሉ፡፡

በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 62 የተዘረዘሩት የም/ቤቱ ስልጣንና ተግባራት የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የሕገ መንግስት አጣሪ ጉባኤን ማደራጀት፣
- የብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች የራስን እድል በራስ የመወሰን እስከ መገንጠል መብትን በተመለከተ የሚነሱ ጥያቄዎች ላይ በሕገ መንግስቱ መሰረት መወሰን፣

- በሕገ መንግስቱ የተደነገገው የህዝቦች እኩልነትና በህዝቦች መፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ አንድነት ስር እንዲሰድና እንዲዳብር ማድረግ፣
- በክልሎች መካከል ለሚነሱ አለመግባባቶች መፍትሔ መፈለግ፣ - የክልሎችና የፌደራሉ መንግስት የጋራ ተብለው የተመደቡ ገቢዎች በሁለቱ መካከል የሚከፋፈልበትን፣ እንዲሁም የፌደራሉ መንግስት ለክልሎች ድጎማ የሚሰጥበትን ቀመር መወሰን፣
- በህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ሕግ ሊወጣላቸው የሚገቡ የፍትሐብሔር ጉዳዮችን መለየት፣
- ማንኛውም ክልል ሕገ ምንግስቱን በመጣስ ሕገ መንግስታዊ ስርዓቱን አደጋ ላይ የጣለ እንደሆነ የፌደራሉ መንግስት ጣልቃ እንዲገባ ማዘዝ፣

-የም/ቤቱን አስፈላጊ ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴዎችን ማቋቋም ናቸው፡፡

የፌደሬሽን ም/ቤት ምልዓተ ጉባኤ የሚኖረው ከአባላቱ ሁለት ሶስተኛው በስብሰባው ላይ ሲገኙ ሆኖ ውሳኔዎች የሚተላለፉት በተገኙት አብላት አብላጫ ድምጽ ነው፡፡ የም/ቤቱ አፈ ጉባኤ የም/ቤቱን ስብሰባዎች ይመራል፡፡ ም/ቤቱ በጀቱን ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት አቅርቦ ያስወስናል፡፡ ም/ቤቱ ቢያንስ በአመት ሁለት መደበኛ ስብሰባዎች ይኖሩታል፤ የም/ቤቱ የስራ ዘመን አምስት አመት ነው፡፡ የፌደሬሽን ም/ቤትና የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ጣምራ አባል መሆን አይቻልም፡፡



## ምዕራፍ 3. የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ አወቃቀር ስልጣንና ተግባር

ሰልጣኞች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፤

- የብሔራዊ የምርጫ ቦርድን አወቃቀር ይገልጻሉ፤
- የብሔራዊ የምርጫ ቦርድን ስልጣንና ተግባራት ይዘረዝራሉ፤
- የምርጫ ክልልን እና የምርጫ ጣቢያን መዋቅራዊ ይዘታ ያብራራሉ፤
- የምርጫ አስፈጻሚዎችን ሃላፊነትና ተግባራት ይዘረዝራሉ።

### ተግባር 3፡- የቡድን ውይይት

**አሰልጣኝ፡-** ተሳታፊዎችን በአራት ቡድን ይክፈሏቸው። ለየቡድኑ የሚከተሉት ጥያቄዎችን ይስጡ።
ቡድን አንድ፡-

1) የብሔራዊ የምርጫ ቦርድ አባላት እንዴት ይመረጣሉ?
2) የብሔራዊ የምርጫ ቦርድ አባላት መምረጫ መስፈርቶች ምን ምን ናቸው?
3) የብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ሃላፊነትና ተግባራት ምን ምን ናቸው?

ቡድን ሁለት፡-

1) የምርጫ ቦርድ የክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች አባላት እንዴት ይመረጣሉ?
2) የምርጫ ቦርድ የክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ሃላፊነትና ተግባራት ምን ምን ናቸው?

ቡድን ሶስት፡-

1) የምርጫ ክልሎች እንዴት ይዋቀራሉ?
2) የምርጫ ክልል ሃላፊነትና ተግባራት ምን ምን ናቸው?

ቡድን አራት፡-

1) የምርጫ አስፈጻሚዎች በምርጫ ሕጉ የተሰጧቸው ስልጣንና ተግባራት ምን ምን ናቸው?

**አሰልጣኝ፡-** እያንዳንዱ ቡድን የተወያየባቸውን የማጠቃለያ ነጥቦች በየተወካዮቻቸው በማቅረብ ተሳታፊዎች አጠቃላይ ውይይት ያካሂዱ። በመጨረሻም የሚከተለው ጽሁፍ ላይ ያሉ ሃሳቦችን በማንጻባረቅ ውይይቱን ይደምድሙ።

### 3.1. የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ አወቃቀር

የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ በ1987 በጸደቀው የኢትዮጵያ ሕገ መንግስት አንቀጽ 102 መሰረት የተቋቋመ ነው። በሕገ መንግስቱ ድንጋጌ መሰረት ‹በፌዴራልና በክልል የምርጫ ክልሎች ነጻና ትክክለኛ ምርጫ በገለልተኝነት እንዲያካሂድ ከማንኛውም ተጽእኖ ነጻ የሆነ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ይቋቋማል፤የቦርዱ አባላት በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅራቢነት በሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ይሾማሉ›። ሕገ መንግስቱ የቦርዱ አጠቃላይ ስልጣንና ተግባር እንዲሁም የአባላቱ አመላመልና አሿሿም በሕግ ይወስናል ባለው መሰረት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁ.1133/2011 እና በኢትዮጲያ የምርጫ ሕጎች ወጥተዋል።

በመጨረሻም ተሻሽሎ የወጣው አዋጅ ቁጥር 532/1999 እስከ 2011 ዓ.ም ድረስ በስራ ላይ ቆይቶ በብሄራዊ የምርጫ ቦርድ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁ. 1133/2011 እና በኢትዮጲያ የምርጫ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ እና የምርጫ ሥነ ምግባር አዋጅ ቁ. 1162/2011 ተተክቷል፡፡

አዋጅ ቁ. 1133/2011 የቦርዱን አባላት አሰያየምም የቦርዱን ተቋማዊ አደረጃጀት እና ሥልጣንና ተግባሮቻቸውን ይመለከታል፤ አዋጅ ቁ. 1162/2011 ደግሞ ዝርዝር የምርጫ ጉዳዮችን የፖለቲካ ፓርቲዎችን ምዝገባ እና ሥነ ምግባር የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን የያዘ ሰፊ ሕግ ነው፡፡ አዋጅ ቁ. 1133/2011 ማዕቀፍ የተደረገው ትልቅ ለውጥ ቀደም ባሉ አዋጆች የቦርዱ አባላት ቁጥር 9 የነበሩና የሙሉ-ጊዜ ሰራተኞች አልነበሩም፡፡ በአዲሱ ሕግ ይህ ሁኔታ ተቀይሮ የቦርዱ አባላት ቁጥር ከ9 ወደ 5 ዝቅ እንዲል የተደረገ ሲሆን የስራ ሁኔታቸውም የሙሉ ጊዜ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ ከ5ቱ አባላት መካከል ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ ይሾማል፡፡

የቦርዱን አባላት አሰያየምም በተመለከተ ጠቅላይ ሚኒሰትሩ እጩ የቦርድ አባላት የሚመለምል ከተለያዩ ተቋማት የተውጣጡ አባላት ያሉት ገለልተኛ ኮሚቴ በማቋቋም ኮሚቴው የእጩዎች ዝርዝር እንዲያቀርብ ተደርጎ በእጩዎቹ ላይ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከተፎካካሪ የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር በቂ ውይይት ካደረገ በኋላ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅርቦ እንደሚያሾም በቦርዱ መልሶ ማቋቋሚያ አዋጅ ውስጥ ተደንግጓል፡፡

አንድ ሰው በቦርድ አባልነት ለመመረጥ በሚሾምበት ጊዜ የማንኛውም ፖሊቲካ ድርጅት አባል ያልሆነና ከፖለቲካ ወገንተኝነት ነጻ የሆነ፣ ከምርጫ ጉዳዮች ጋር ተያያዥነት ባላቸው በተለይም በሕግ፣ በፖሊቲካል ሳይንስ፣ በሕዝብ አስተዳደር፣ በእስታቲስቲክስ፣ በኢንፎርሜሽን ተክኖሎጂ እና ሌሎች ተዛማጅነት ባላቸው ዘርፎች ከፍተኛ ሞያዊ ብቃት ያለው፣ መልካም ስነ ምግባር እና ሰብእና ያለው፣ እንዲሁም የቦርዱ አባላት ስብስብ በሃገሪቱ ያለውን ብሄራዊና የጾታ ተዋጽኦ ያገናዘበ እንዲሆን ሕጉ ይደነግጋል፡፡

ቦርዱ ጽህፈት ቤት እንደሚኖረው ሕጉ ይደነግጋል፡፡ ጽ/ቤቱ በቦርዱ ጉባኤ የሚሾሙ አንድ ዋና ኃላፊና በአንድ ምክትል ኃላፊ ይመራል፡፡ ቦርዱ በሁሉም ክልሎች ምርጫ የሚያስተባብር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ይኖረዋል፡፡ የክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሃላፊዎች ቦርዱ በሚያወጣው መመርያ መሰረት ገለልተኛነታቸውና ሙያዊ ብቃታቸው ከተረጋገጠ የክልሉ ነዋሪዎች መካከል በቦርዱ ሰብሳቢ አቅራቢነት በቦርዱ ጉባኤ ይሰየማሉ፡፡ ቦርዱ የክልሎችን የቆዳ ስፋት፣ የህዝቡን አሰፋፈርና የመራጮችን ብዛት መሰረት በማድረግ ለክልል ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች ተጠሪ የሆኑ እንደ አግባብነቱ የዞን እና የምርጫ ክልል ማስተባበሪያ በቋሚነት ሊያቋቁም እንደሚችልና የነዚህን ማስተባበሪያ ጽ/ቤቶች አሰራር፣ ተግባራትና ኃላፊነቶች ቦርዱ በሚያወጣው ደንብ መወሰን እንደሚችል ሕጉ ይደነግጋል፡፡

### 3.2. የቦርዱ የክልል ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት

በሁሉም ክልሎች እና ሁለቱ የከተማ አስተዳደሮች ምርጫን የሚያስተባብሩ የቦርዱ የክልል ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች ይቋቋማሉ፡፡ የቦርዱ የክልል ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት በቦርዱና በቦርዱ ሰብሳቢ እንዲሁም እንደ አግባብነቱ በቦርዱ ጽህፈት ቤት ሃላፊ አጠቃላይ መመሪያና አቅጣጫ እየተሰጠው ይሰራል፡፡ በዚሁ መሰረት የሚከተሉትን ተግባርና ኃላፊነቶች ያከናውናል፡

1) በክልል ደረጃ የሚካሄደውን ምርጫ ይመራል፤ያስተባብራል፤ይቆጣጠራል፤
2) በስሩ የሚቋቋሙት ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤቶች ስለሚደራጁበት ሁኔታ ለቦርዱ ጽህፈት ቤት ሀሳብ ያቀርባል፡፡
3) ለምርጫ የሚያስፈልጉ ሰነዶችና ቁሳቁሶች ለሚመለከታቸው ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤቶችና የምርጫ ክልልና ጣቢያዎች በወቅቱ መድረሳቸውን ይከታተላል፣ያረጋግጣል፤

4) ከቦርዱ በሚሰጠው መመሪያ መሰረት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የስነ ዜጋና የመራጮች ትምህርት ይሰጣል፣ያስተባብራል፣
5) የመራጮች አመዘጋገብ፣ የእጩዎች አቀራረብና የድምጽ አሰጣጥ ስርዓት ህጉ በሚፈቅደው መሰረት እየተካሄደ መሆኑን ይከታተላል፣ይቆጣጠራል።
6) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 በተጠቀሱት ጉዳዮች ላይ የሚነሱትን ቅሬታዎችና ተቃውሞዎች በክልል ደረጃ እየመረመረ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ይወስናል።
7) የክልሉን የምርጫ ሂደትና ውጤት በሚመለከት ለቦርዱ ጽህፈት ቤት ሪፖርት ያቀርባል፡
8) ለምርጫ አፈጻጸም በሚያመች መልኩ አግባብ ያላቸውን መረጃዎች እየሰበሰበና እያጠና በየጊዜው ለቦርዱ ጽህፈት ቤት ሪፖርት ያቀርባል።
9) ስለስራ እንቅስቃሴው በየወቅቱ ለቦርዱ ጽህፈት ቤት ሪፖርት ያቀርባል፣
10) የስራ አመራር ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት በክልል እና በምርጫ ጣቢያ ደረጃ የፖለቲካ ድርጅቶች የጋራ መድረክ እንዲዋቀር ያደርጋል፣በክልል የሚቋቋሙ የፖለቲካ ድርጅቶች የጋራ መድረክ ያስተባብራል፤
11) የክልሉ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይቋቋማል።

ከላይ በቀረቡት የቦርዱና የቦርዱ የክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ተግባርና ኃላፊነት ወስጥ እንደተመለከተው ከክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በታች የዘን፣ የምርጫ ክልል እንዲሁም የምርጫ ጣቢያ ማስተባበርያ ጽ/ቤቶችን ቦርዱ በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት ሊያደራጅ እንደሚችል ሕጉ ይደነግጋል።

### 3.3. የምርጫ ክልሎች

በኢትዮጵያ የምርጫ ሕግ የምርጫ ክልሎች የሚደራጁት የክልሎች ወሰን እንደተጠበቀ ሆኖ ወረዳን መሰረት በማድረግ በቋሚነት ነው። የምርጫ ክልሎቹ በሕዝብ ቆጠራ ውጤት መሰረት በየጊዜው ማስተካከያ ሊደረግባቸው ይችላል። በሕገ መንግስቱ ላይ እንደተደነገገው የአገሪቱ የምርጫ ክልሎች ብዛት ከ550 መብለጥ የለበትም። የሕገ መንግስቱ አንቀጽ 103(5) እንዳስቀመጠው በየአስር ዓመቱ በሚደረገው የህዝብ ቆጠራ ውጤት መሰረት የምርጫ ክልሎች አከላለል የምርጫ ቦርድ በሚያቀርበው ረቂቅ መሰረት በፌደሬሽን ምክር ቤት ይወሰናል። በየደረጃው የሚካሄዱ የአከባቢ ምርጫዎችን የምርጫ ክልሎች በተመለከተ ለየም/ቤቶቹ የሚመረጡትን አባላትና የመራጩን ብዛት መሰረት በማድረግ በክልሉ ሕግ መሰረት የምርጫ ክልሎች ይወሰናሉ፡

**የምርጫ ክልል፤**

- ቦርዱ በሚያወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት የምርጫ ቁሳቁሶችን ለምርጫ ጣቢያዎች ያሰራጫል፣ እጩዎችን ይመዘግባል፣መታወቂያ ይሰጣል፣
- ከምርጫ ጣቢያዎች የሚመጡ ሰነዶችና የምርጫ ቁሳቁሶች በአግባቡ ተሞልተው መምጣታቸውን ያረጋግጣል፣ ይረከባል፣ በጥንቃቄ እንዲያዙ ያደርጋል፣
- ምርጫ ጣቢያዎች ተግባራቸውን በአግባቡ ማከናወናቸውን ይቆጣጠራል፣
- በህግ መሰረት ለሚቀርቡ ቅሬታዎችና አቤቱታዎች ውሳኔ ይሰጣል፣
- ከምርጫ ጣቢያ የመጡ የምርጫ ውጤቶችን በማዳመር አሸናፊዎችን ከለየ በኋላ ውጤቱን ለህዝብ ይፋ በማድረግ አስፈላጊ ቅጾችን በመሙላት ለቦርዱ ይልካል፣
- ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት የተመራጭነት መታወቂያ ካርድ ለአሸናፊዎች ይሰጣል፣
- የእጩ ወኪሎችን ዝርዝር ለምርጫ ጣቢያዎች ያስተላልፋል፣

- የምርጫ ክልሉን አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት በዚህ ሕግ እና ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ያስመርጣል፣
- በምርጫ ክልሉ የሚወዳደሩ የፖለቲካ ድርጅቶችን የጋራ መድረክ ሊያደራጅ ይችላል።

### 3. 4. የምርጫ ጣቢያዎች

የምርጫ ጣቢያዎች ቦርዱ አካል ጉዳተኞችን ጨምሮ የተለያዩ ታሳቢዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት በሚወስነው ስፍራ የሚቋቋም ሲሆን አድራሻቸውም የመራጮች ምዝገባ ከመጀመሩ ከ15 ቀናት አስቀድሞ ለሕዝብ ይፋ መሆን እንዳለበት አዋጅ ቁ. 1162/2011።ሆኖም፤የአርብቶ አደር ህዝብ በሚኖርበት አከባቢ ተንቀሳቃሽ የምርጫ ጣቢያዎች ሊቋቋሙ ይችላሉ። ቦርዱ የምርጫ ጣቢያዎችን ከለወጠ ለመራጩ ይህንኑ ማስታወቅ ይኖርበታል።



የምርጫ ጣቢያዎች የመራጮች ምዝገባ፣ የድምጽ መስጫ እና የቆጠራ ጣቢያ ሆነው ያገለግላሉ። በምርጫ ሕጉ ላይ የምርጫ ጣቢያ ሆነው ማገልገል የሚችሉ ቦታዎች ተለይተው ተመልክተዋል። በዚሁ መሰረት፤ወታደራዊ ካምፖች፣የፖሊስ ጣቢያዎች፣አብያተ ክርስቲያናት እና መስጊዶች፣ ሆስፒታሎችመጠጥ ቤቶች፣ የፖሊቲካ ወይም የኃይማኖት ድርጅቶች ህንጻዎች፣ መኖርያ ቤቶች የምዝገባና የድምጽ መስጫ ስፍራ በመሆን ሊያገለግሉ አይችሉም።

**የምርጫ ጣቢያ ቦርዱ በሚያወጣው ደንብና የጊዜ ሰሌዳ መሰረት፡**

- መራጮችን ይመዘግባል፣
- ከምርጫ ክልሉ የሚላኩ የምርጫ ቁሳቁሶችን በጥንቃቄ እንዲያዙ ያደርጋል፣
- ምርጫ ያካሂዳል፣
- በሕግ መሰረት የሚቀርቡ ቅሬታዎችን ያስተናግዳል፣
- የተሰጠውን ድምጽ በመቁጠርና የምርጫ ውጤትን በማስታወቂያ ሰሌዳ በማውጣት ለህዝብ ያሳውቃል፣
- የምርጫ ሰነዶች እና ቁሳቁሶች በአግባቡ ተሞልተው እና ተጠብቀው ለምርጫ ክልሉ እንዲላኩ ያደርጋል፣

እያንዳንዱ የምርጫ ጣቢያ የሚያስተናግደው የመራጮች ብዛት ከ1ሺህ 500 መብለጥ እንደሌለበትና ለአንድ የምርጫ ጣቢያ በተከለለ አካባቢ ከአንድ የምርጫ ጣቢያ በላይ ማቋቋም እንደማይቻል ሕጉ ይደነግጋል።ምርጫ ቦርድ ከምርጫ ክልላቸው ርቀው በካምፕ የሚኖሩ ወታደሮችና ሲቪል ሰራተኞች እንዲሁም በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚማሩ ዜጎች በምርጫ የሚሳተፉበትን ሁኔታ ለማመቻቸት መራጮች በሚገኙበት ቦታ ወይም አከባቢ ልዩ ምርጫ ጣቢያ ሊያቋቁም ይችላል።

### 3.5. የምርጫ አስፈጻሚዎች ተግባርና ኃላፊነቶች

ምርጫ ነጻ፣ ተዓማኒና ሰላማዊ እንዲሆን የምርጫ አስፈጻሚዎች ሚና እጅግ በጣም ከፍተኛ ነው። የዴሞክራሲ ባህል ባልዳበረባቸውና በፖለቲካ ኃይሎች መካከል መተማመን በሌለባቸው አገራት ለሰላም ዋስትና ሊሆኑ ከሚችሉ ነገሮች ውስጥ ዋነኛው የምርጫዎች በገለልተኛና በተዓማኒ የምርጫ አስፈጻሚዎች መከናወን ነው። ስለዚህ የምርጫ አስፈጻሚዎች ፍጹም ገለልተኛና ብቃት ያላቸው መሆን ይኖርባቸዋል።

ቀደም ሲል በዚሁ ምዕራፍ ስር እንደተመለከትነው ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ገለልተኛ ብቃትና የህዝብ ተአማኒነት ያላቸው የምርጫ አስፈጻሚዎች በቦርዱ ጽ/ቤቶች መመልመላቸውን፣መቀጠራቸውንና መሰልጠናቸውን የማረጋገጥ ስልጣንና ኃላፊነት በሕግ ተሰጥቶታል፡፡ ቦርዱ እነዚህ ሰራተኞች ከማናቸውም አካል የሚደርስባቸውን ተጽእኖ ሊከላከልላቸው እንደሚገባ የምርጫ ሕጉ ይደነግጋል፡፡

የምርጫ እስፈጻሚዎች በምርጫ ክልልና በምርጫ ጣቢያ ጽ/ቤቶች በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት ምርጫን ለማስፈጸም በቦርዱ ተቀጥረው የሚሰሩ ሰራተኞች ናቸው፡፡ በዚሁ መሰረት እያንዳንዱ ምርጫ ጣቢያ ገለልተኛ፣ ተአማኒና የሙያ ብቃት ያላቸው 5 የምርጫ አስፈፃሚዎችን የያዘ ኮሚቴ ይኖረዋል፡፡ የምርጫ ጣቢያው ሃላፊ ኮሚቴውን በሰብሳቢነት ይመራል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ እያንዳንዱ የምርጫ ክልል ከላይ የተጠቀሱትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ሶስት ሰዎችን የያዘ የምርጫ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይኖረዋል፡፡

የምርጫ እስፈጻሚዎች በምርጫ ሕጉ ከተሰጧቸው ስልጣንና ተግባራት መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡

- በስፋቱና በዓይነቱ የምርጫውን ውጤት ሊያዛንፍ የሚችል በምርጫ ሂደት የተፈፀመ የህግ መጣስ፣ የማጭበርበር፣ ወይም የሰላምና ፀጥታ ማደፍረስ ድርጊት መከሰቱን ያመኑ ከሆነ ሁኔታውን ለምርጫ ቦርድ ማሳወቅ፣
- በምርጫ ክልልና በምርጫ ጣቢያ ደረጃዎች በሚቋቋሙት የአቤቱታ ሰሚ ኮሚቴዎች በአባልነት መሳተፍ፣
- ከፖለቲካ ድርጅት እና የግል እጩ ወኪሎች፣ የህዝብ ታዛቢዎች እና ፣ ስነስርአት አስተባባሪዎች ጋር በመሆን የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱ በሕጉ የተመለከቱተን ስርዓቶች በተከተለ መንገድ መጀመሩን ማረጋገጥ፤ በተለይ ደግሞ የምርጫ ጣቢያ ኃላፊው የድምፅ መስጫ ሳጥኑ ባዶ መሆኑን ቀደም ሲል ለተገለጹት አካላት በማሳየት የምርጫ ሳጥኑ በተዘጋጀው ማሸጊያ ከታሸገ በኋላ በታዛቢዎች ፊት ለፊት በቅርብ እይታና በግልጽ ስፍራ መቀመጡን ወይም መሰቀሉን ካረጋገጠ በኋላ ስለአጀማመሩ ቃለጉባዔ ተይዞ ቦርዱ ለዚሁ ተግባር ባዘጋጀው ቅፅ ላይ ከተሞላ በኋላ ቆጠራ እንዲጀመር መደረጉን ማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡
- የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ ማንኛውም ሰው በስካር ወይም በሌላ ምክንያት የምርጫ ጣቢያውን ሰላም የሚያደፈርስ ከሆነ ወይም መግባት የሌለበት ሰው ምርጫ ጣቢያ ወስጥ ገብቶ ሂደቱን ካወከ ሰውየው እንዲወጣ ማዘዝንና ፖሊስ መጥራትን ጨምሮ በዚህ ሁኔታ ላይ እርምጃ እንዲወሰድ የማድረግ ስልጣን አለው፤ ይህንኑ ማድረግ ይኖርበታል፡፡
- ማንኛውም ህገ ወጥ መጽሐፍ ይዞ በምርጫ ጣቢያ ስለመገኘቱ አሳማኝ ጥቆማ የቀረበበትን ሰው የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ የሁሉም የፖለቲካ ድርጅት እና የግል እጩ ወኪሎች እንዲሁም የህዝብ ታዛቢዎች በተገኙበት ተጠርጣሪውን ሊፈትሽ ይችላል፤ተጨባጭ ሆኖ ከተገኘም አስፈላጊው ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፤
- በምርጫ እለት ለመምረጥ የመጡ መራጮችን ትክክለኛ መራጮች መሆናቸውን ማረጋገጥ፣
- የምርጫ ታዛቢዎችንና የእጩ ወኪሎችን በተገቢውና በሕጋዊ መንገድ ማስተናገድ፣
- በድምጽ አሰጣጥ ሂደት የድምጽ መስጫ ወረቀት ከተበላሸ፤ ስለመበላሸቱ ምልክት በማድረግና በመለየት ለዚሁ በተዘጋጀ ሳጥን ውስጥ እንዲከተቱ ማድረግ፣
- የድምጽ አሰጣጥ ሂደት በማንኛውም ምክንያት ከተቋረጠና ሁኔታው መልሶ ከተስተካከለ የምርጫ አስፈፃሚዎች ይህንኑ ሁኔታ በቃለ ጉባኤ ይዘው ወዲያውኑ የድምፅ አሰጣጡ ሂደት እንዲቀጥል ማድረግ፤ ነገር ግን የምርጫ ሂደቱን ያስተጓጎለው ጉዳይ ከአቅም በላይ ከሆነና ምርጫው መቀጠል ካልቻለ በቃለ ጉባኤ ተይዞ የድምፅ አሰጣጥ ሂደቱ ባለበት ቆሞ ወዲያውኑ አጠቃላይ ሁኔታው ለበላይ ምርጫ ጽህፈት ቤት ሪፖርት እንዲደረግ ማድረግ፣

- በድምጽ አሰጣጥ ሂደት ላይ ለሚነሱ ቅሬታዎች በቅሬታ ሰሚ ኮሚቴው በኩል መልስ እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣
- ለድምፅ መስጫ ወረቀቶች ከፍተኛ ጥንቃቄና ጥበቃ የማድረግ ሕጋዊ ግዴታቸውን መወጣት ይኖርባቸዋል፡፡
- የምርጫ ሕጉ በሚያዘው መሰረት ማንኛውም የምርጫ ሰነድ ከአንዱ ሰው ወደ ሌላው ሰው በሚተላለፍበት ጊዜ ህጋዊ የርክክብ ስርዓትን ተከትሎ መፈፀሙን ማረጋገጥ፣
- አስገዳጅ በሆነ ምክንያት የምርጫ ድምጽ ቆጠራው በምርጫ ጣቢያ ደረጃ መከናወን ካልቻለ የምርጫ ጣቢያው የምርጫ አስፈፃሚ ለምርጫ ክልሉ ጥያቄ አቅርቦ ሲፈቀድ ወይም የምርጫ ክልሉ የምርጫ አስፈፃሚ ሲወስን ቆጠራው በምርጫ ክልሉ ጽህፈት ቤት በሚካሄድበት ጊዜ በምርጫ ክልሉ ጽህፈት ቤት የሚካሄደው ቆጠራ የምርጫ ጣቢያው የእጩ ወኪሎችና የህዝብ ታዛቢዎች በተገኙበት መሆኑን ማረጋገጥ፡፡

**የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ የድምፅ ቆጠራ ከመጀመሩ በፊት፡**

- ✓ የድምፅ መስጫው ሳጥን እሽግ ያልተከፈተ እና ድምፅ መስጠት ከመጀመሩ በፊት በታሸገበት ሁኔታ መቆየቱን፣ ሳጥኑም ያልተቀደደና ብልሽት ያልደረሰበት መሆኑን የእጩ ወኪሎች እና የህዝብ ታዛቢዎች ካረጋገጡ እና ቃለጉባኤ ከተያዘ በኋላ እሽጉ እንዲከፈት ያደርጋል፤ ድምፅ የተሰጠባቸው ወረቀቶች በሙሉ ወጥተው ሳጥኑም ባዶ መሆኑ ይረጋገጣል፣
- ✓ የእጩ ወኪሎች እና የህዝብ ታዛቢዎች ባሉበት በዕለቱ ድምፅ የሰጡ መራጮችን ብዛት እና የተበላሹና ስራ ላይ ያልዋሉ የድምፅ መስጫ ወረቀቶችን ብዛት መመዘግብ አለበት፡፡
- ✓ የድምጽ ቆጠራው እንደተጠናቀቀ የእጩ ተወካዮችና የህዝብ ታዛቢዎች ስለድምጽ አሰጣጡ እና የቆጠራው ሂደት ትክክል መሆን አለመሆን፣ ቅሬታ ያለው ወግን ቅሬታወን እንዲያስመዘግብ ተደርጎ ቃለ ጉባኤ ተይዞ፣ መፈረም ያለባቸው አካላት ፈርመው እና አስፈላጊው ቅጽ በትክክል ተሞልቶና ተፈርሞ ሰነዶቹ ታሽገው ወደ ምርጫ ክልል መላካቸውን የምርጫ ጣቢያ የምርጫ አስፈጻሚዎች ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡
- ✓ በምርጫ ጣቢያ የተደረገ የቆጠራ ውጤት ቆጠራው በተጠናቀቀ በአንድ ሰዓት ውስጥ በምርጫ ጣቢያው ማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ወጥቶ ለህዝብ በይፋ መገለጹን ማረጋገጥ፤ የምርጫ ክልል ጽ/ቤትም ከየምርጫ ጣቢያው ውጤት እንደደርሷቸው ተወዳዳሪዎች ወይም ወኪሎቻቸው በተገኙበት አዳምረው የተገኘውን ውጤት ለህዝብ ይፋ ማድረግ እና የውጤቱንም መተማመኛ ለተወዳዳሪዎች ወይም ወኪሎቻቸው መስጠት እንዲሁም ለቦርዱ ጽ/ቤትና በየደረጃው ላሉ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እንዲደርስ ማድረግ ይኖርበታል፡፡



እንግዲህ ከላይ የተዘረዘሩት መጠነ ሰፊ የምርጫ አስፈጻሚዎች ሚናዎች በትክክል ከተከናወኑ እነዚህ አካላት አጠቃላይ ምርጫው ፍትሐዊ፣ ነጻ፣ ገለልተኛ፣ ተዓማኒና ሰላማዊ እንዲሆን ሊተካ የማይችል ሚና እንደሚጫወቱ ማየት ይቻላል፡፡ ስለሆነም ተገቢ የሙያ ስነምግባር ያላቸውና በገለልተኝነታቸው የታወቁ የምርጫ አስፈጻሚዎች መመልመላቸውን የምርጫ ቦርድ ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም የምርጫ አስፈጻሚዎች የስራቸውን ዝርዝር ሁኔታና የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት በትክክል እንዲረዱ በቂ ስልጠና ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

## ምዕራፍ 4.   የምርጫ ሕግጋትና እና የምርጫ ሂደቶች በኢትዮጵያ

ሰልጣኞች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፤

- የኢትዮጵያ የምርጫ ስርዓትን ይገልጻሉ፤
- በኢትዮጵያ የሚካሄዱ የምርጫ ዓይነቶችን ይዘረዝራሉ፤
- ምርጫ በኢትዮጵያ ዲሞክራሲ ግንባታ ላይ ያለውን አስተዋጽዖ ያብራራሉ፤

**ተግባር 4.1፡- አጠቃላይ ውይይት**

**አሰልጣኝ፡-** የሚከተሉትን ጥያቄዎችን በማንሳት ተሳታፊዎች ውይይት እንዲያደርጉ ይጋብዙ፡፡

1) በኢትዮጵያ የሚካሄዱ የምርጫ አይነቶች ምንምምን ናቸው?
2) ምርጫ በኢትዮጵያ ዲሞክራሲ ግንባታ ላይ ያለውን አስተዋጽዖ ምንድን ነው?

**አሰልጣኝ፡-** የሚከተለው ጽሁፍ ላይ ያሉ ሃሳቦችን በማንጸባረቅ ውይይቱን ይደምድሙ፡፡

### 4.1. የኢትዮጵያ የምርጫ ስርዓትና የሚካሄዱ የምርጫ አይነቶች

በኢትዮጵያ 5 የምርጫ አይነቶች ይካሄዳሉ፡፡ እነሱም፡ 1) ጠቅላላ ምርጫ፣ 2) የአካባቢ ምርጫ፣ 3) ማሟያ ምርጫ፣4) ድጋሚ ምርጫ፣ እና 5) ህዝበ ውሳኔ ናቸው፡፡

**ጠቅላላ ምርጫ** ፡- ይህ ምርጫ በየአምስት ዓመቱ የሚካሄድ የህዝብ ተወካዮች እና የክልል ምክር ቤቶች አባላት ምርጫ ነው፡፡ ጠቅላላ ምርጫ በመላ ሀገሪቱ በተመሳሳይ ጊዜ ይካሄዳል፡፡ ሆኖም ቦርዱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው እና ጉዳዩ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርቦ ውሳኔ ሲያገኝ በተለያየ ጊዜ እንዲካሄድ ሊያደርግ ይችላል፡፡

**የአካባቢ ምርጫ**፡-ደግሞ በህግ በተደነገገው መሰረት በየደረጃው በሚገኙ የዘን፣የወረዳ፣ የከተማ፣ የማዘጋጃ ቤት፣ የክፍለ ከተማ ወይም የቀበሌ ምክር ቤቶች አባላት ምርጫ ነው፡፡ በአካባቢ ምርጫ በአንድ ምርጫ ክልል ምን ያህል ተወካዮች እንደሚመረጡ እንደየ ምርጫው ዓይነትና ለየምክርቤቱ የሚመረጡትን አባላት መሰረት በማድረግ በየክልሎቹ ህግ ይወሰናል፡፡ የአካባቢ ምርጫ ምንም እንኳን ዝቅተኛ መስፈርቶችን በተመለከተ የፌዴራሉ የሕግ አውጪ ምክር ቤት ሕግ ሊያወጣ እንደሚችልና የክልል ሕጎች የሕገ መንግስቱንና የአዋጅ ቁ.1162/2011ን መስፈርቶች ያሟሉ መሆን እንዳለባቸው ተደንግጓል፡፡

**የማሟያ ምርጫ**፡-የሚካሄደው በየደረጃው ያሉ ምክር ቤቶች በተለያየ ምክንያት የተጓደሉባቸው አባላት እንዲሟሉላቸው ለቦርዱ ጥያቄ ሲያቀርቡ ወይም በህጉ መሠረት የቀረበ የተወካይ ይነሳልን ጥያቄ ተቀባይነት ሲያገኝ ነው፡፡ ነገር ግን አንድ ምክር ቤት የስራ ዘመኑ ሊያልቅ ስድስት ወራት የቀረው ከሆነ የማሟያ ምርጫ አይካሄድም፡፡

**ድጋሚ ምርጫ**፡- ከሚካሄድባቸው ምክንያቶች ውስጥ አንዱ በምርጫው ሂደት በተከሰተ የሕግ መጣስ ወይም ማጭበርበር ወይም የሰላም መደፍረስ ምክንያት የምርጫው ውጤት ተዛብቷል ብሎ ቦርዱ ሲወስን ነው፡፡ ሌላው ምክንያት እጩ ተወዳዳሪዎች እኩል ድምፅ በማግኘታቸው ምክንያት አሸናፊውን መለየት አስቸጋሪ በሆነ ጊዜ ነው፡፡ ሆኖም ድጋሚ ምርጫ ሲካሄድ ሌላ አዲስ የመራጩች ምዝገባ ሳያስፈልግ በምርጫ ክልሉ ወይም ችግሩ የተከሰተባቸው የምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ ተመዝግበው በነበሩ መራጮች ይካሄዳል፡፡ በተጨማሪም ድጋሚ ምርጫ እንዲካሄድ ሲወሰን አዲስ የእጩዎች ምዝገባ ሳያስፈልግ ቀድሞ በተመዘገቡ እጩዎች መካከል ብቻ እንዲካሄድ ይደረጋል፡፡ በድጋሚ ምርጫ ሂደት የምርጫ ቅስቀሳ አይደረግም፡፡

**ሕዝበ ውሳኔ** ፡- በህገ መንግስቱ መሰረት አግባብ ባለው አካል ሲወሰን የህዝብን ፍላጎት ለመለካት ወይም ለመወሰን ድምጽ የሚሰጥበት ስርአት ነው፡፡ ህዝበ ውሳኔው እንዲካሄድ የወሰነው አካል በሚሰጠው መመሪያ መሰረት የምርጫ ቦርድ ህዝበ ውሳኔ ያስፈለገበትን ጉዳይ ለመለየት በሚያስችለው መልኩ የድምጽ መስጫ ጣቢያዎችን በማደራጀት ህዝበ ውሳኔውን ያከናውናል፡፡

## 4.2. ምርጫና ዴሞክራሲ

የውክልና ዴሞክራሲ የሚተገበረው የተለያዩ የፖሊሲ አማራጮችን ይዘው ከቀረቡ የፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል መራጩ ህዝብ ይበጀኛል የሚለውን ሲመርጥና የአሸናፊው ፓርቲ (ፓርቲዎች) ተወካይ ወይም ተወካዮች ደግሞ የሕግ አውጪውንና የሕግ እስፈጻሚውን ለተመረጡበት የምርጫ ዘመን ተረክበው ሲያስተዳድሩ ነው፡፡

ይህ የሕዝብ ውክልና በሕግ በተቀመጠው መሰረት በየጊዜው በተወሰነለት የጊዜ ሰሌዳ መታደስ ይኖርበታል፡፡ ይህም ማለት በኢትዮጵያ ወስጥ በየደረጃው ያሉ የም/ቤት ተወካዮች ምርጫ በየ5 አመቱ የሚካሄድ ስለሆነ የህዝብ ውክልና የሚታደሰው በየአምስት አመቱ ነው ማለት ነው፡፡ ይህ የሚያሳየው ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት መተግበር ምርጫ የማይተካ ሚና የሚጫወት መሆኑን ነው፡፡

የዴሞክራሲ ዋና መገለጫ ሕዝብ በተወካዮቹ አማካኝነት እራሱን በራሱ የሚያስተዳድርበት ስርዓት ነው፡፡ የሕዝብ ተወካዮች ደግሞ የሚመረጡት ለዚሁ ተብለው በሚዘጋጁ ምርጫዎች አማካኝነት ነው፡፡ ለዚህም ነው ዴሞክራሲን ያለ ምርጫ ማሰብ አይቻልም የሚባለው፡፡

ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ በቀለም፣ በዘር፣በብሔር፣ በብሔረሰብ፣ በጾታ፣በቋንቋ፣ በኃይማኖት፣በፖለቲካ ወይም በሌላ አመለካከት ወይም በሌላ አቋም ላይ የተመሰረተ ልዩነት ሳይደረግበት የሚከተሉት መብቶች አሉት፡-

ሀ) በቀጥታና በነጻነት በመረጣቸው ተወካዮች አማካኝነት በህዝብ ጉዳይ አስተዳደር የመሳተፍ፣
ለ) እድሜው 18 አመት ሲሞላ በሕግ መሰረት የመምረጥ፣
ሐ) በማናቸውም የመንግስት ደረጃ በየጊዜው በሚካሄድ ምርጫ የመምረጥና የመመረጥ፡፡

ምርጫው ሁሉአቀፍ፣ በሁሉም እኩልነት ላይ የተመሰረተና በሚስጥር ድምጽ አሰጣጥ መራጩ ፈቃዱን በነጻነት የሚገልጽበት ዋስትና የሚሰጥ መሆን አለበት፡፡

## 4.3. ለመራጮች ስለሚሰጡ የምርጫ መረጃዎች

ለመራጮች የሚሰጥ መረጃ ከዋናው የምርጫ ትምህርት/ስልጠና ይለያል፡፡ ለመራጮች የሚሰጥ መረጃ አንድ ስለምርጫ ተሳትፎ በቂ እውቀት ያለው ሰው ከአጭር ጊዜ በኋላ ለሚደረግ ምርጫ ወይም ምርጫዎች ወሳኝ የሆኑ ቅድመ ዝግጅቶች ሳያልፉትና አስፈላጊ ሰነዶችን ይዞ ያለ ውጣ ውረድ መምረጥ እንዲችል የሚረዳ ነው፡፡ በዚሁ መሰረት የሚከተሉት ጠቃሚ ከሆኑ የመራጮች መረጃዎች ወስጥ የሚካተቱ ናቸው፡፡

1) የመራጮች ምዝገባ መቼ እንደሚጀመርና የት መመዝገብ እንደሚቻል የሚገልጽ መረጃ፣
2) በመራጭነት ለመመዝገብ ወደ ምርጫ ጣቢያ ምን ምን ሰነዶች ይዞ መሄድ እንዳለበት፣
3) በምዝገባ ሂደት ችግር ቢገጥመው ወይም ደግሞ ሕገ ወጥ የሚመስል ነገር ቢያይ እንዴትና ለማን ቅሬታ ማቅረብ እንዳለበት፣
4) የምርጫው እለት መቼ እንደሆነ፤ በዕለቱ የምርጫ ጣቢያው ለምን ያህል ሰዓታት ክፍት እንደሚሆን፣

5) በካምፕ የሚኖሩ ወታደሮች/በከፍተኛ የትምህርት ተቋም ያሉ ተማሪዎች ከሆኑ የት መመዝገብና መምረጥ እንዳለባቸው፣
6) የአካል ጉዳተኛ ለሆኑ ወይም ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው መራጮች ምዝገባ የሚደረግበት ቦታ ሁኔታና ሊያገኙ የሚችሉት ድጋፍ፣
7) የአካል ጉዳተኛ ለሆኑ ወይም ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው መራጮች የምርጫው ዕለት እንዴት ድጋፍ ሊያገኙ እንደሚችሉ የሚሉት ናቸው።

**ተግባር 4.2፡- አሳታፊ የምርጫ ድራማ (Mock Election)**

**አሰልጣኝ፡-** ከምርጫ ምዝገባ ጀምሮ ያሉትን የመራጭነትና የተመራጭነት እስከ ውጤት ገለጻ ያሉትን ሂደቶች የሚያሳይ አሳታፊ ድራማ (Mock Election) ቀደም ሲል በተዘጋጁ ወጣቶች (የተቀረጸውን ቪዲዮ) እንዲቀርብ ያድርጉ። ከድራማው በኋላ ተሳታፊዎች ከድራማው የተማሯቸውን ነጥቦች ከመራጮች፣ ከተመራጮች፣ ከምርጫ አስፈጻሚዎችና ከሌሎችም ከሚመለከታቸው አካላት አንጻር እያነሱና እንዲዘረዝሩ ይጠይቋቸው። በመጨረሻም የሚከተለው ጽሁፍ ላይ ያሉ ሃሳቦችን በማንጸባረቅ ውይይቱን ይደምድሙ።

## 4.4. የመራጮች ምዝገባ

በማንኛውም ምርጫ ለመሳተፍ አስቀድሞ በመራጭነት መመዝገብ ቅድመ ሁኔታ ነው። አንድን ሰው በመራጭነት ለመመዝገብ የሚያበቁት መስፈርቶችና የሚያስፈልጉት ሰነዶች በምርጫ ሕግና እንደ አስፈላጊነቱም በምርጫ ቦርድ በሚወጡ ዝርዝር ደንቦችና መመርያዎች ይቀመጣሉ። ነገር ግን እነዚህ መስፈርቶች ተገቢና አሰፈላጊ በሆነ መጠን ብቻ እንጂ እንድን ሰው ያለ አግባብ ከመራጭነት የሚያገሉ መሆን የለባቸውም።

በአዋጅ ቁ. 1162/2011 መሠረት በማንኛውም ምርጫ፡-

- ኢትዮጵያዊ የሆነ ሰው፣
- በምዝገባው ዕለት ዕድሜው 18 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነና
- ለምዝገባ በቀረበበት የምርጫ ክልል ቢያንስ ለ6 ወራት የኖረ ሰው በመራጭነት ለመመዝገብ ይችላል።

ነገር ግን በአዕምሮ በህመም ምክንያት የመወሰን አቅም የሌለው መሆኑ የሚታወቅ ሰው፣ በፍርድ የተወሰነበትን የእስራት ቅጣት በመፈጸም ላይ ያለ ሰውና የመምረጥ መብቱ በሕግ የተገደበበት ሰው በመራጭነት ለመመዝገብ እንደማይችል በሕጉ ተደንግጓል።

የመራጮች ምዝገባ የሚከናወነው በምርጫው ዓይነት ላይ ተመስርቶ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ በሚያወጣው የመራጮች ምዝገባ የጊዜ ሰሌዳ አማካኝነት ሲሆን የምዝገባ ቦታውም መራጮች በሚኖሩበት ቀበሌ በሚቋቋም



የምርጫ ጣቢያ ብቻ ነው። ሆኖም በአርብቶ አደር አከባቢዎች አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ተንቀሳቃሽ የመራጮች ምዝገባ ማዕከላት በማቋቋም የመራጮችን ምዝገባ ማከናወን ይቻላል። አንድ ሰው ለመራጭነት በአንድ የምርጫ ጣቢያ መመዝገብ የሚችለውአንድ ጊዜ ብቻ ነው። እያንዳንዱ የምርጫ ጣቢያ የራሱ የመራጮች መዝገብ ይኖረዋል።

**የመራጮች ምዝገባን በተመለከተ ሁለት ሊታወሱ የሚገባቸው ጉዳዮች፤**

1) የመራጮች ምዝገባ ሊከናወን የሚችለው ቦርዱ በሚያወጣው የጊዜ ሰሌዳ ውስጥ ብቻ ነው።
2) ቀደም ሲል እንደተገለጸው ለአርብቶ አደር አከባቢዎች በተለየ ሁኔታ ካልተወሰነ በስተቀር ምዝገባው የሚከናወነው መራጮች በሚኖሩበት ቀበሌ በሚቋቋም የምርጫ ጣቢያ ብቻ ነው።

አንድ መራጭ በመራጭነት ተሳትፎ የሚፈልገውን ፓርቲ ወይም ዕጩ ተወዳዳሪ ለመምረጥ የሚችለው በቅድሚያ በመራጭነት ሲመዘገብ ብቻ ነው። በመራጭነት ሳይመዘገብ ቀርቶ በምርጫው ዕለት መራጭ ሆኖ መቅረብ አይችልም። ስለሆነም ቦርዱ ስለመራጮች ምዝገባ መጀመር በልዩ ልዩ የብዙኀን መገናኛዎች ሲገልጽ በመከታተልና በመመዝገብ የመራጭነት መብትን በእጅ ማስገባት ያሰፈልጋል።

**አንድ ሰው ለመራጭነት ለመመዝገብ ወደ ምርጫ ጣቢያ በሚመጣበት ጊዜ የሚከተሉትን ሰነዶች መያዙን ማረጋገጥ ይኖርበታል፤**

በምርጫ ጣቢያው ክልል ውስጥ ነዋሪ መሆኑን የሚገልጽ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት፤ ከነዚህ አንዱም ከሌሉት ሌሎች የማንነት መግለጫ ሰነዶችን (መንጃ ፈቃድ፣ የመኖሪያ የምስክር ወረቀት፣ በተባበሩት መንግስታት የተሰጠ የስደተኛ ካርድና የመሳሰሉት) መያዝ ይችላል።

ሆኖም ካላይ የተጠቀሱት ሰነዶች ባይኖሩትም ለመመዝገብ የቀረበውን ሰው መዝጋቢዎቹ በአከባቢው ነዋሪ መሆኑን ለይተው የሚያውቁት ከሆነ ወይም በምርጫ ጣቢያው በህዝብ የተመረጡ የህዝብ ታዛቢዎች የሚያወቁት ከሆነ በቃለ-ጉባኤ ተይዞ መመዘገብ ይችላል።

በተለያየ ምክንያት ራሳቸውን ችለው መመዝገብ የማይችሉ ሰዎች በረዳቶቻቸው አማካኝነት በአካል ተገኝተው መመዝገብ ይችላሉ።

የመራጮች መዝገብ፤ የየዕለቱ ምዝገባ ሲጠናቀቅ በዕለቱ የመጨረሻው ተመዝጋቢ የተመዘገበበት ተራ ቁጥርና ቀን ለዚሁ በተዘጋጀ ቅጽ ላይ ከተሞላ በኋላ መዝጋቢዎችና የሕዝብ ታዛቢዎች በጋራ ይፈራረሙበታል። ይህ ድርጊት የመራጮች ምዝገባ እስከሚጠናቀቅበት ቀን ድረስ በየዕለቱ የሚከናወን ይሆናል። የመራጮች ምዝገባ በሚጠናቀቅበት ዕለትም ከመጨረሻው ተመዝጋቢ ቀጥሎ ባለው ትርፍ ቦታ ላይ መዝጋቢዎችና የሕዝብ ታዛቢዎች ተፈራርመውበት መዝገቡ ይዘጋል። የመራጮች መዝገብ በዚህ መልኩ ከተዘጋ በኋላ በምርጫ ቦርድ በተለየ ሁኔታ ካልተወሰነ በስተቀር አዲስ መራጭ ሊመዘገብበት አይችልም።

የምርጫ ሂደት ከተጠናቀቀ በኋላ የመራጮች መዝገብ በምርጫ ጣቢያው ቅጥር ግቢ ውስጥ ለ10 ተከታታይ ቀናት በህዝብ እንዲታይ (እንዲመረመር) ይደረጋል። ምዝገባን የሚመለከት ማናቸውም ተቃውሞ በማንኛውም ሰው ወይም የፖለቲካ ድርጅት ለምርጫ ጣቢያው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ሊቀርብ ይችላል።

በተመሳሳይ ሁኔታ አንድ ሰው በመራጭነት እንዳይመዘገብ የሚያግደው ሁኔታ ከገጠመው ለምርጫ ጣቢያው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ጉዳዩን አቅርቦ ውሳኔ የማግኘት መብት አለው። በመራጭነት መመዝገብ የሌለበት ሰው ወይም መብት የሌለው ሰው ያለአግባብ ተመዝግቧል የሚል ሰው ወይም የፖለቲካ ድርጅት ተቃውሞውን ለምርጫ ጣቢያ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ የማቅረብ እና ውሳኔ  የማግኘት መብት አለው።

በመራጭነት የተመዘገበ ሰው በአዕምሮ ሕመም ምክንያት ለመወሰን ብቃት የሌለው ሆኖ የተገኘ ወይም በማጭበርበር የተመዘገበ ወይም የሞተ ወይም የተፈረደበት ካልሆነ በስተቀር በማናቸውም ሌላ ምክንያት ከመራጭነት መዝገብ አይሰረዝም።

### 4.5. የእጩዎች ምዝገባ

የዕጩዎች ምዝገባ ከምርጫው ዕለት ቢያንስ 90 ቀን አስቀድሞ የኢትዮጲያ ብሄራዊ የምርጫ ቦርድ በሚያወጣው የምዝገባ የጊዜ ሰሌዳ መሰረት በየምርጫ ክልሉ ይከናወናል፡፡ በጠቅላላ ምርጫ በምርጫ ጣቢያ የዕጩ ምዝገባ አይካሄድም፡፡

### 4.6. ስለ ምርጫ ዘመቻ

አንድ ዕጩ ተወዳዳሪ በዕጩነት ተመዝግቦ መታወቂያውን ካገኘበት ቀን አንስቶ ምርጫው አራት ቀን እስኪቀረው ድረስ ከአስተዳደሩም ሆነ ከማዘጋጃ ቤት ፈቃድ ሳይጠይቅ በፅሁፍ በማሳወቅ ብቻ ህጋዊ ግዴታዎቹን በማክበር በራሱም ሆነ በደጋፊዎቹ አማካይነት የድጋፍ ስብሰባዎችን የመጥራት ወይም ሰላማዊ ሰልፍ የማደራጀት መብት አለው፡፡ እንዲሁም ለምርጫ ውድድሩ ይጠቅሙኛል ያላቸውን መረጃዎች ከቦርዱ የማግኘት መብት ይኖረዋል፡፡ የምርጫ ውድድር እንቅስቃሴ ህገመንግስቱና አግባብነት ያላቸውን ሌሎች ህጎች፣ የመራጮችን መብት፣ የሌሎች እጩዎችን የመወዳደር መብት በማክበር በሰላማዊና በዴሞክራሲያዊ መንገድ መካሄድ አለበት፡፡

እጩዎችና ደጋፊዎቻቸው ቦርዱ በሚያወጣው ደንብ መሰረት የሚያካሂዱት የምርጫ ውድድር እንቅስቃሴ ድምጽ መስጠት ከመጀመሩ ከ 4 ቀናት በፊት መጠናቀቅ አለበት፡፡

በመንግስት ቁጥጥር ስር ያሉት የመገናኛ ብዙሃን ማለትም ሬድዮ፣ ቴሌቪዥንና ጋዜጦች ለምርጫ ዘመቻ የሚውሉበትን ሁኔታ አስመልክቶ በምርጫ ሕጉ እንደተደነገገው የእጩ ደጋፊ የሆኑት የፖለቲካ ድርጅቶችና የህብረተሰብ ክፍሎች እነዚህን የመገናኛ ብዙሃን ያለ አድልዎ የመጠቀም መብት አላቸው፡፡ እጩዎችም በመንግስት የመገናኛ ብዙሃን ነፃ የአየር ጊዜ አግኝተው የመጠቀም መብት አላቸው፡፡ የመንግስት መገናኛ ብዙሃን አጠቃቀም የሚመለከተው የመንግስት ኃላፊ ከቦርዱ ጋር በመሆን የፖለቲካ ድርጅቶች እንዲያውቁት ከተደረገና አስተያየት ከሰጡበት በኋላ በሚያወጣው ድልድል መሰረት ይከናወናል፡፡ በተጨማሪም በማንኛውም ደረጃ የሚገኙ የመንግስት አካላት ኃላፊዎች የምርጫ ውድድር እንቅስቃሴ እንዲሳካ ለማድረግ በየሃላፊነታቸው ስር የሚገኙትን የሬድዮ ጣቢያዎች፣ የስብሰባ አዳራሾች፣ ጋዜጦችና የመሳሰሉትን ዕጩዎችና ደጋፊዎቻቸው ያለአድልዎ ለመጠቀም የሚያስችላቸው ሁኔታ የማመቻቸት ግዴታ እንዳለባቸው የምርጫ ሕጉ ይደነግጋል፡፡

### 4.7. ስለድምፅ አሰጣጥ

የድምጽ መስጠት ሂደት በሁሉም ምርጫ ጣቢያዎች ቦርዱ በሚወስነው ቀን አንድ ላይ ይጀመራል፡፡ ነገር ግን አስገዳጅ ሁኔታ በሚያጋጥምበት ጊዜ የሚመለከታቸው ምርጫ ጣቢያዎች ስራቸውን በተለየ ቀን እንዲጀምሩ ቦርዱ ሊወስን እንደሚችል የምርጫ ሕጉ ይደነግጋል፡፡



የምርጫጣቢያዎች የድምፅ የድምጽ አሰጣጡ ስራ የፖለቲካ ድርጅት እና የግል እጩ ወኪሎች፣ የህዝብ ታዛቢዎች፣ የምርጫ አስፈፃሚዎች እና ስነስርአት አስተባባሪዎች በተገኙበትና የምርጫ ጣቢያ ኃላፊው የድምፅ መስጫ ሳጥን ባዶ መሆኑን በማሳየት የምርጫ ሳጥኑ በተዘጋጀው ማሸጊያ ታሽጎ በታዛቢዎች ፊት ለፊት በቅርብ እይታና በግልጽ ስፍራ ከተቀመጠ ወይም ከተሰቀለ በኋላ ስለአጀማመሩ ቃለጉባዔ ተይዞ ቦርዱ ለዚሁ ተግባር ባዘጋጀው ቅፅ ላይ ከተሞላ በኋላ ይጀመራል፡፡ የምርጫጣቢያዎች የድምፅ መስጫ ዕለት ከመድረሱ በፊት አስተማማኝ የደህንነት ጥበቃ ተደርጎላቸው መዘጋጀት አለባቸው፡፡

ቦርዱ በተለየ ሁኔታ ካልወሰነ በስተቀር የድምጽ መስጫ ሰዓት ከጠዋቱ 12 ሰዓት እስከ ምሽቱ 12 ሰአት ድረስ ይሆናል። ቦርዱ በተለየ ሁኔታ የድምፅ መስጫ ሰዓት የወሰነ እንደሆነ በልዩ ሁኔታ የተወሰነውን የድምፅ መስጫ ሰአት ቢያንስ ከ2 ቀናት በፊት ህዝቡ በይፋ እንዲያውቀው ያደርጋል። የድምጽ መስጫ ሰአት ሲያበቃ የምርጫ ጣቢያው ይዘጋል። ሆኖም በምርጫ ጣቢያው ቅጥር ግቢ ውስጥ ገብተው ድምፅ ለመስጠት በመጠባበቅ ላይ ያሉ መራጮች ድምፅ መስጠት አለባቸው። ነገር ግን ቦርዱ የምርጫውን ነፃና ፍትሃዊነት ይበልጥ ያሰፍናል ብሎ ካመነ የድምፅ መስጫ ሰአትን ሊያራዝም ይችላል።

የምርጫ ጣቢያዎች ለምርጫ ከመከፈታቸውም ሆነ ድምፅ አሰጣጡ አልቆ ከተዘጉ በኋላ ከምርጫ አስፈፃሚዎች፣ ከህዝብ ከተመረጡ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት፣ ከእጩ ተወካዮች እና ከተፈቀደላቸው የምርጫ ታዛቢዎች በስተቀር ማንኛውም ሰው ወደ ምርጫ ጣቢያው መግባት አይችልም።

### የድምፅ አሰጣጥ መስፈርትን በተመለከተ የምርጫ ሕጉ የሚከተለውን ይደነግጋል፤

1. ማንኛውም መራጭ በአካል በመገኘት በሙሉ ነፃነት ድምፅ ይሰጣል።
2. እያንዳንዱ መራጭ ድምፅ የሚሰጠው አንድ ጊዜ ብቻ ይሆናል።
3. ማንኛውም መራጭ ድምፅ ለመስጠት የሚችለው በመራጭነት በተመዘገበበት የምርጫ ጣቢያ ብቻ ሆኖ፡-
    ሀ. የመራጮች መታወቂያ ካርድ ሲኖረው፣
    ለ. በመራጮች መዝገብ ላይ ስሙ ሰፍሮ ሲገኝ፣ እና
    ሐ. ድምፅ ያልሰጠ መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው።

### የድምፅ አሰጣጥ ሂደት

1) እያንዳንዱ መራጭ የመራጮች ምዝገባ መታወቂያ ካርዱን ለምርጫ ጣቢያው የምርጫ አስፈፃሚዎች ካስረከበ በኋላ የምርጫ አስፈፃሚዎቹ የመራጩን ማንነት ባቀረበው ማስረጃ ይለያሉ። 2) የመራጩ ማንነት ከተለየና ቀደም ሲል ያልመረጠ መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ በመራጮች መዝገብ ውስጥ ለፊርማ በተዘጋጀው አምድ ላይ እንዲፈርም ይደረጋል።

3) መራጩ በመዝገብ ላይ ከፈረመ በኋላ አውራ ጣቱን፣ አውራ ጣት ከሌለው ማንኛውንም ሌላ ጣት በተዘጋጀው የማይለቅ ቀለም እንዲቀባ ከተደረገ በኋላ የድምፅ መስጫ ወረቀት ተሰጥቶት ወደ ሚስጢር ድምፅ መስጫው ክፍል ይገባል።

4) መራጩ ወደ ምስጢር ድምጽ መስጫው ክፍል ገብቶ የሚመርጠው እጩ መለያ ምልክት በሚገኝበት ባለአራት ማዕዘን ቦታ ላይ የ"x" ምልክት ካደረገበት ወይም በጣት አሻራው ከፈረመበት በኋላ የድምጽ ማስጫ ወረቀቱን አጥፎ በታዛቢዎች ፊት ለፊት በቅርብ እይታ በግልጽ ስፍራ በተቀመጠው የድምፅ መስጫ ሳጥን ወይም ኮሮጆ ውስጥ ይከታል።

5) የማያነቡና የማይፅፉ መራጮች ከጣቶቻቸው አንዱን ለዚህ በተዘጋጀው ቀለም ከነከሩ በኋላ ከሚመርጡት ዕጩ መለያ ምልክት ትይዩ በሚገኘው ባለ አራት ማዕዘን ክፍት ቦታ ላይ የጣት አሻራቸው እንዲያርፍ በማድረግ ድምፅ ይሰጣሉ።

6) መራጩ የተሰጠውን የድምፅ መስጫ ወረቀት ባግባቡ ሳይጠቀምበት የቀረ ወይም የተበላሸበት እንደሆነ ይህንኑ መልሶ በምትኩ ሌላ በመቀበል ድምፅ ለመስጠት ይችላል።

7) የምርጫ ጣቢያ ኃላፊ ተበላሽቶ ተመላሽ የተደረገውን የድምፅ መስጫ ወረቀት የተለየ ምልክት ወይም የተበላሸ የሚል በጀርባው ላይ አድርጎበት ለዚሁ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ይከተዋል፡፡

በምርጫ ድምፅ አሰጣጥ ምልክት ለማድረግና የድምፅ መስጫ ወረቀቱን ወደ ድምፅ መስጫው ሳጥን ወይም ኮሮጆ ውስጥ ለመክተት እርዳታ የሚያስፈልገው ማንኛውም መራጭ የሚረዳውን ሰው እራሱ የመወሰን መብት አለው፡፡ ነገር ግን በድጋፍ ፈላጊው የተመረጠው ሰው ዕድሜ 18 አመት እና ከዚያ በላይ ሆኖ እጩ ወይም የእጩ ተወካይ መሆን የለበትም፡፡



በምርጫው ዕለት ድምጽ የመስጠት ሂደት ከተጀመረ ሊቋረጥ ወይም ሊቆም አይችልም፡፡ ሆኖም ግን የድምፅ አሰጣጡ ሂደት በተለያየ ምክንያት ለጥቂት ጊዜም ቢሆን ከተቋረጠና ሁኔታው መልሶ መስተካከሉን የምርጫ አስፈፃሚዎች ካመኑ ሁኔታው በቃለ ጉባኤ ተይዞ ወዲያውኑ የድምፅ አሰጣጡ ሂደት ሊቀጥል ይችላል፡፡ በሌላ በኩል የድምፅ አሰጣጥ ሂደቱ የተቋረጠበት ሁኔታ ከአቅም በላይ ሆኖ ሊስተካከል ካልቻለ ሁኔታው በቃለ ጉባኤ ተይዞ የድምፅ አሰጣጥ ሂደቱ ባለበት እንዲቆም ተደርጎ አጠቃላይ ሁኔታው ለምርጫ ክልል ጽ/ቤት ሪፖርት ይደረጋል፡፡ በዚህ ሁኔታ የተቋረጠ የድምፅ አሰጣጥ ሂደት ቦርዱ በሚወስነው መሰረት በሌላ ጊዜ ይካሄዳል፡፡

በድምፅ መስጠት ሂደት  የሚቀርብ ተቃውሞን በሚመለከት ድምጽ በመስጠት ላይ ያለ መራጭ የድምጽ መስጫ ወረቀቱን ከመስጠቱ በፊት የእጩ ተወካይ ድምፅ በመስጠት ሂደት ላይ ያለው ሰው የመራጭነት መብት የሌለው ወይም በምርጫ ጣቢያው በመራጭነት ያልተመዘገበ ነው በማለት ተቃውሞ ሊያቀርብበት ይችላል (ሆኖም አቤቱታው እስኪጣራ ድረስ የምርጫ ጣቢያው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ አቤቱታ የቀረበበት መራጭ በጊዜያዊነት ድምጽ እንዲሰጥ ሊወስን ይችላል)፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ አንድ መራጭ የድምፅ መስጫ ወረቀት ቢከለከል እራሱ ወይም ከእጩ ተወካዮች አንዱ ተቃውሞ ሊያቀርብ ይችላል፡፡ የእጩ ተወካይ ወይም አንድ መራጭ  ከላይ ከተገለጹት የመቃወሚያ ነጥቦች ውጭ በምርጫ አስፈፃሚው፣ የእጩ ተወካይ ወይም በሌላ በማንኛውም ሰው አግባብ ያልሆነ ድርጊት በምርጫ ጣቢያው ውስጥ ተፈጽሟል ብሎ ተቃውሞ ሊያቀርብ ይችላል፡፡ የምርጫ ጣቢያው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ከላይ የቀረበውን አቤቱታ ከተመለከተ በኋላ ተገቢውን ማጣራት አድርጎ አቤቱታ ላቀረበው ሰው ወይም አካል ውሳኔውን ያሳውቃል፡፡

## ስለ ድምፅ መስጫ ወረቀት

1. ቦርዱ ለእያንዳንዱ የምርጫ አይነት መራጩ በግልጽ ሊረዳው የሚችል እስከተቻለ ድረስ ለማጭበርበር የማይመች የድምፅ መስጫ ወረቀት ያዘጋጃል፡፡
2. ቦርዱ የእጩዎች ፎቶግራፍ፣ የእጩ መለያ ምልክት፣ የእጩዎች ሙሉ ስምና የፖለቲካ ድርጅታቸው መጠሪያ የታተመበት የድምፅ መስጫ ወረቀት ሊያዘጋጅ ይችላል፡፡
3. ቦርዱ በየምርጫ ጣቢያው በተመዘገበው መራጭ ቁጥር ልክ እና ለመጠባበቂያ የሚሆን የተወሰነ ቁጥር ያለው የድምጽ መስጫ ወረቀት ይልካል፡፡
4. ቦርዱ እና በየደረጃው ያሉ የምርጫ አስፈፃሚዎች ለድምፅ መስጫ ወረቀቶች ከፍተኛ ጥንቃቄና ጥበቃ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡
5. ማንኛውም የምርጫ ሰነድ ከአንዱ ሰው ወደ ሌላው ሰው በሚተላለፍበት ጊዜ ህጋዊ የርክክብ ስርዓትን ተከትሎ መፈፀም አለበት፡፡

### 4.8. የድምጽ ቆጠራና ውጤት አገላለጽ

የድምጽ መስጠት ሂደቱ እንደተጠናቀቀ ቆጠራው መከናወን አለበት። ይህንኑ አስመልክቶ የምርጫ ሕጉ አስገዳጅ በሆነ ምክንያት የምርጫ ጣቢያው የምርጫ አስፈፃሚ ለምርጫ ክልሉ ጥያቄ አቅርቦ ሲፈቀድ ወይም የምርጫ ክልሉ የምርጫ አስፈፃሚ ወስኖ ቆጠራው በምርጫ ክልሉ ጽህፈት ቤት ካልተካሄደ በስተቀረ የማንኛውም ምርጫ ድምፅ ቆጠራ የሚካሄደው ድምፅ በተሰጠበት ምርጫ ጣቢያ ነው በማለት ይደነግጋል። በተከሰተው አስገዳጅ ምክንያት ቆጠራው በምርጫ ክልል ጽ/ቤት የሚካሄድ ከሆነ ቆጠራው መካሄድ ያለበት የምርጫ ጣቢያው የእጩ ወኪሎችና የህዝብ ታዛቢዎች በተገኙበት ይሆናል።

ድምፅ ቆጠራ ከመጀመሩ በፊት የድምፅ መስጫው ሳጥን እሽግ ያልተከፈተ እና ድምፅ መስጠት ከመጀመሩ በፊት በታሸገበት ሁኔታ መቆየቱን፣ ሳጥኑም ያልተቀደደና ብልሽት ያልደረሰበት መሆኑን የእጩ ወኪሎች እና የህዝብ ታዛቢዎች ካረጋገጡ እና ቃለጉባኤ ከተያዘ በኋላ እሽጉን በመክፈት ድምፅ የተሰጠባቸው ወረቀቶች በሙሉ ይወጣሉ። ሳጥኑም ባዶ መሆኑ ይረጋገጣል። የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ ቆጠራ ለመጀመር የእጩ ወኪሎች እና የህዝብ ታዛቢዎች እንዲገኙ በማድረግ በዕለቱ ድምፅ የሰጡ መራጮችን ብዛትና የተበላሹና ስራ ላይ ያልዋሉ የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ብዛትን ይመዘግባል።

ከዚያ ለእያንዳንዱ ዕጩ ድምጽ የተሰጠባቸው ወረቀቶች ተለይተው ይቆጠራሉ። ምርጫው የተካሄደው ለተለያዩ ምክር ቤቶች ከሆነ በመጀመርያ ለየምክር ቤቱ የተሰጡት የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ከተለዩ በኋላ በንዑስ አንቀፅ 3 መሰረት የአንዱ ምክር ቤት ተቆጥሮ እንዳለቀ የሌላው በመቀጠል ይቆጠራል። የድምፅ ቆጠራ ሂደት በቦርዱ ውሳኔ ካልሆነ በስተቀር ሊቋረጥ ወይም ሊቆም አይችልም። ሆኖም ቆጠራ ለመጀመር የሚያስችል በቂ ብርሃን የሌለ ዕንደሆነ የዕጩ ወኪሎች ከሕዝብ የተመረጡ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት እና የምርጫ ጣቢያ ኃላፊ ይህንኑ በመግለፅ ቃለ ጉባኤ ይፈራረማሉ።ይህም ሲሆን ሁሉም የድምፅ መስጫ ወረቀቶች አስፈላጊው የጥበቃ ኃይል እንዲኖር በማድረግ ደኅንነታቸው በተረጋገጠ ሁኔታ እንዲያድሩ ይደረጋል።የተቋረጠው የድምፅ ቆጠራ ሒደት በሚቀጥለው ቀን እጅግ ቢዘገይ ከጠዋቱ 1 ሰዓት ጀምሮ  መካሄድ ይኖርበታል።

**በድምጽ መስጠት ወቅት ድምፅ የተሰጠባቸው ወረቀቶች፡**

1) የመራጩ ማንነት በስም የተገለፀበት ከሆነ፣

2) ከተመራጮች ቁጥር በላይ ምልክት የተደረገበት ከሆነ፣

3) ምንም ምልክት ያልተደረገበት ከሆነ፣

4) መራጩ ማንን እንደመረጠ መለየት የሚያስቸግር ከሆነ፣

5) ህጋዊ የድምፅ መስጫ ወረቀት ያልሆነ ወይም በምርጫ ጣቢያው ያልተሰራጨ የድምፅ መስጫ ወረቀት ከሆነ ዋጋ አልባ ይሆናሉ። ከነዚህ በአንዱ ምክንያት ዋጋ አልባ የተደረጉ ወረቀቶች በጀርባቸው "ውድቅ" የሚል ፅሁፍ ተፅፎባቸው ለብቻቸው ተቆጥረው መታሸግ አለባቸው።

የድምጽ ቆጠራው እንደተጠናቀቀ የእጩ ተወካዮችና የህዝብ ታዛቢዎች ስለድምጽ አሰጣጡ እና የቆጠራው ሂደት ትክክል መሆን አለመሆን፣ ቅሬታ ያለው ወግን ቅሬታውን እንዲያስመዘግብ ተደርጎ ቃለ ጉባኤ ተይዞ፣ መፈረም ያለባቸው አካላት ፈርመው እና አስፈላጊው ቅጽ በትክክል ተሞልቶና ተፈርሞ ሰነዶቹ ታሽገው ወደ ምርጫ ክልል ይላካሉ።  በምርጫ ጣቢያ የተደረገ የቆጠራ ውጤት ቆጠራው በተጠናቀቀ በአንድ ሰዓት ውስጥ በምርጫ ጣቢያው ማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ወጥቶ ለህዝብ በይፋ መገለጽ አለበት። የምርጫ ክልል ጽ/ቤትም ከየምርጫ ጣቢያው ውጤት እንደደረሷቸው ተወዳዳሪዎች ወይም ወኪሎቻቸው በተገኙበት አዳምረው የተገኘውን ውጤት

ለህዝብ ይፋ ማድረግ እና የውጤቱንም መተማመኛ ለተወዳዳሪዎች ወይም ወኪሎቻቸው መስጠት እንዲሁም ለቦርዱ ጽ/ቤትና በየደረጃው ላሉ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እንዲደርስ መደረግ ይኖርበታል።

**የአጠቃላይ የቆጠራ ውጤትን አገላለፅ በተመለከተ የምርጫ ሕጉ (አንቀጽ 76) የሚከተለውን ይደነግጋል፤**



1) በምርጫ ጣቢያ የተደረገ የቆጠራ ውጤት ቆጠራው በተጠናቀቀ በአንድ ሰዓት ውስጥ በምርጫ ጣቢያው ማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ወጥቶ ለህዝብ በይፋ ይገለፃል።

2) የምርጫ ክልል የምርጫ ጽህፈት ቤቶች የህዝብ ተወካዮችና የክልል ምክር ቤቶች አባላት ምርጫ ውጤት ከየምርጫ ጣቢያው እንደደረሳቸው ተወዳዳሪዎች ወይም ወኪሎቻቸው በተገኙበት አዳምረው የተገኘውን ውጤት ለህዝብ ይፋ ያደርጋሉ።

3) እጩ ተወዳዳሪዎች እኩል ድምጽ በማግኘታቸው ምክንያት አሸናፊውን ለመለየት አስቸጋሪ የሆነ እንደሆነ እኩል ድምፅ ያገኙት ተወዳዳሪዎች ብቻ ተለይተው ቦርዱ በሚወስነው ጊዜ ድጋሚ ምርጫ እንዲካሄድ ይደረጋል።

4) የምርጫ ክልል የምርጫ ኃላፊዎች ከላይ በንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ይፋ ያደረጉትን ውጤት፡-
  ሀ) ለተወዳዳሪዎች ወይም ወኪሎቻቸው የውጤት መተማመኛ ይሰጣሉ፣
  ለ) በውጤት ማሳወቂያ ቅፅ ሞልተው አንድ ቅጂ ለቦርዱ ጽህፈት ቤት እና በየደረጃው ለሚገኙ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች ይልካሉ።

5) ቦርዱ በአጠቃላይ የምርጫ ውጤት ከየምርጫ ክልሉ ተጠናቆ እስኪደርሰው ድረስ ከየምርጫ ክልሉ የመጣለትን የህዝብ ተወካዮችና የክልል ምክር ቤቶች አባላት የምርጫ ውጤት በጊዜያዊነት በቦርዱ ጽህፈት ቤት ይፋ ሊያደርግ ይችላል።

6) ከላይ በንዑስ አንቀፅ (2) የተጠቀሰው አሰራር ለአካባቢ ምርጫ ውጤትም እንደሁኔታው ተግባራዊ ይሆናል።

**ይፋዊ መግለጫ**

የምርጫው ሂደት ከተጠናቀቀና አስፈላጊ መረጃዎች ከተሰበሰቡ በኋላ ቦርዱ ይፋ ባወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱትን ነጥቦች የያዘ ይፋዊ መግለጫ ያወጣል።

1. የተመዘገቡ መራጮች ቁጥር ፣
2. ድምፅ የሰጡ መራጮች ቁጥር፣
3. ድምፅ የሰጡና ያልሰጡ ተመዝጋቢ መራጮች መጠን በመቶኛ፣
4. የተመረጡ እጩዎች የስም ዝርዝርና የተመረጡበት የምርጫ ክልል፣
5. የአሸናፊ ፖለቲካ ድርጅቶች ስምና ለየምክር ቤቱ ያሸነፉትን መቀመጫ ብዛት፣
6. ጥቅም ላይ የዋለ፣ ያልዋለ፣ ከጥቅም ውጭ የሆነ የድምፅ መስጫ ወረቀት እያንዳንዱ እጩ በየምርጫ ጣቢያው ያገኘው የድምፅ ውጤት እና ሌሎች ዝርዝር መረጃዎች ከየምርጫ ክልሉ እንደደረሰው እና አጠናቅሮ እንደጨረሰ ይፋ ያደርጋል።

## ምዕራፍ 5. በዴሞክራሲያዊ ምርጫ የዜጎች መብቶችና ኃላፊነቶች

ሰልጣኞች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፤

- ኢትዮጵያውያን በምርጫ ጉዳይ ያላቸውን መብት ይዘረዝራሉ፤
- በኢትዮጵያ በሚካሄዱ ምርጫዎች የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ሊኖራቸው ስለሚገባው ተሳትፎ ይገልጻሉ፤

**ተግባር 5፡- አጠቃላይ ውይይት**

**አሰልጣኝ፡-** የሚከተሉትን የግለሰብ ሃሳቦች በጽሁፍ ለተሳታፊዎች ይስጡና ወይም በንባብ ያቅርቡላቸውና አጠቃላይ ውይይትን ይጋብዙ።

ሀ) <ያደለውማ ይመርጣል! እኛን ማን ያስታውሰናል።> – የጉልት ነጋዴዋ እማማ ወርቄ፤ <ካርድ ወሰዱ?> ተብለው ሲጠየቁ፤

ለ) <ነፍሰጡር ብሆንም መምረጥማ አለብኝ።> – የ8 ወር ነፍስጡሯ አለሚቱ፤ <በሰላም መገላገልሽ እንጂ ምርጫው ምንሽ ነው?>ላላት ባለቤቷ፤

ሐ) <ምርጫ ጣቢያው ለሁሉም አመቺ መሆን ይገባዋል።> – የምርጫ ጣቢያ መግቢያ ላይ ካለ ደረጃ ትይዩ ድልድይ እያሰራ ላለና<አንተ የዊልቼር ተጠቃሚ አይደለህም ምን አለፋህ?> ለተባለ የምርጫ አስፈጻሚ፤

መ) <ምርጫን በመታዘብ ተሳታፊነትን ማረጋገጥ ይቻላል።> – አንድ ታዛቢ<በዚህ ምርጫ እንዴት ትሳተፋለህ> ተብሎ ሲጠየቅ፤

በመጨረሻም የሚከተለው ጽሁፍ ላይ ያሉ ሃሳቦችን በማንጸባረቅ ውይይቱን ይደምድሙ።

### 5.1. በዴሞክራሲያዊ ምርጫ የዜጎች መብቶች

ይህ መብት የኢትዮጵያ ሕገ መንግስት በአንቀጽ 38(1)(ሀ) ስር ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ያለምንም ልዩነት ‹በቀጥታና በነጻነት በመረጣቸው ተወካዮች አማካኝነት በህዝብ ጉዳይ አስተዳደር የመሳተፍ› መብት አለው በማለት በደነገው መብት ውስጥ የሚታቀፍ ነው። በሌላ አነጋገር ህዝቡ በመረጣቸው እንደራሴዎች አማካኝነት እራሱን በራሱ የሚያስተዳድርበት መብት ነው ይህ መብት። ስለዚህ ዜጎች ምርጫ በአንድ ወይ በሌላ መልኩ የህልውና ጉዳይ መሆኑን ተገንዝበው በነቂስ ወጥተው ድምጽ መስጠት ብቻ ሳይሆን ትክክለኛና ተዓማኒ ምርጫ እንዲካሄድ ከታች እንደምንመለከተው በተለያየ መንገድ ተጨማሪ ኃላፊነታቸውንም መወጣት ይኖርባቸዋል።

### በዴሞክራሲያዊ ምርጫ ሂደት የዜጎች መብቶች ምን ምንድን ናቸው?

የኢትዮጵያ ሕገ መንግስት የአገሪቱ ዜጎች በዴሞክራሲያዊ ምርጫ ሂደት ያሏቸውን ተጨማሪ መብቶች በአንቀጽ 38 በዝርዝር አስቀምጧል። በዚሁ መሰረት የመጀመርያውና ዋነኛው መብት የመምረጥና የመመረጥ መብትን አፈጻጸም በተመለከተ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ በቀለም፣ በዘር፣ በብሔር፣ በብሔረሰብ፣ በጾታ፣በቋንቋ፣ በኃይማኖት፣በፖለቲካ ወይም በሌላ አመለካከት ወይም በሌላ አቋም ላይ የተመሰረተ ልዩነት አይደረግበትም የሚለው ነው። ይህ መብት አንድ ኢትዮጵያዊ በማናቸውም የአገሪቱ ክፍሎች በተዘረዘሩት የመድሎ ምክንያቶች ላይ የተመሰረተ ልዩነት ሳይደረግበት የመምረጥና የመመረጥ መብት ያለው መሆኑን ያረጋግጣል።

በኢትዮጵያ ሕገ መንግስት የተረጋገጠው የምመረጥና የመመረጥ መብት አንድ መራጭ የሚመርጠውን ፓርቲ ወይም እጩ በሚስጥር የመምረጥ መብት ያለው መሆኑን ይደነግጋል። ይህ መብት በኢትዮጵያ የምርጫ ቦርድ

(እና በመንግስት) ላይ በተጓዳኝነት መራጩ ድምጽ በሚስጥር ለመስጠት የሚያስችለውን አካባቢያዊና ቴክኒካዊ ሁኔታ የማሟላት ግዴታ ይጥላል፡፡

## 5.2. በዴሞክራሲያዊ ምርጫ የዜጎች ከመምረጥ መመረጥ ውጪ ባሻገር

በዴሞክራሲያዊ የምርጫ ሂደት ዜጎች በመራጭነት እና በተመራጭነት ከመሳተፍ በተጨማሪ ተሳትፎ የሚያደርጉባቸው ብዙ የኃላፊነት መድረኮች አሉ፡፡ ከነዚህም ውስጥ በምርጫ ታዛቢነት መሳተፍ እና በምርጫ አስፈጻሚነት መሳተፍ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

### ዜጎች በምርጫ ታዛቢነት የሚያደርጉት ተሳትፎ

የኢትዮጵያ የምርጫ ሕግ ታዛቢዎችን በሁለት ይከፍላቸዋል፡፡ እነዚህም፤

1) የአገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢዎች፣ እና
2) የውጭ የምርጫ ታዛቢዎች፣

**የአገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢዎች** የሚባሉት በአገሪቱ ውስጥ የተቋቋሙትና የሚንቀሳቀሱት የሲቪል ማሕበራት ሲሆኑ እነዚህ የሲቪል ማሕበራት በሕጉ የተመለከቱትን ስርዓቶች ተከትለው ከቦርዱ በሚያገኙት ይሁንታ የምርጫውን ሂደት መታዘብ ይችላሉ፡፡ እነዚህ ማህበራትና የሚያሰማሯቸው ግለሰብ ታዛቢዎች ለማንም የፖለቲካ ድርጅት ወይም እጩ ያልወገኑ መሆኑንና ለዚህም የገለልተኛ ታዛቢነት ስነ ምግባር መተማመኛ ይፈርማሉ፡፡

**የውጭ የምርጫ ታዛቢዎች** የውጭ መንግስታት ተወካዮች፣ የአለም አቀፍ ድርጅቶች፣የአህጉራዊና ክፍለአህጉራዊ ድርጅቶች ተወካዮች እና በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጪ የሚንቀሳቀሱ መንግስታዊ ወይም መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተወካዮች በራሳቸው ጠያቂነት ወይም በኢትዮጵያ መንግስት ግብዣ የምርጫ ሂደቶችን የሚመለከቱ ታዛቢዎች ናቸው፡፡

ሁለቱም የምርጫ ታዛቢ ዘርፎች፤ የሚያሳተፏቸው ታዛቢዎች ቀደም ሲል እንደተገለጸው ገለልተኛ መሆንና ለማንኛውም ተወዳዳሪ የማይወግኑ መሆን አለባቸው፡፡ በተጨማሪም ተገቢውን ተግባራቸውን ለመወጣት የሚያስችላቸው በቂ ስልጠናና ዝግጁነት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ በመሆኑም የምርጫ ታዛቢዎችን በተመለከተ ሕጋዊ ኃላፊነት ያለበት የምርጫ ቦርድ የምርጫ ታዛቢዎች በቂ የሆነ ሞያዊና ስነ-ልቦናዊ ዝግጅት ማድረጋቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

ከሁለቱ ታዛቢዎች በተጨማሪ በምርጫ ወቅት እጩ ያቀረቡ የፖለቲካ ፓርቲዎችና የግል ተወዳዳሪዎች የምርጫውን ሂደቶች የሚከታተሉላቸው የራሳቸው ተቀማጭና ተዘዋዋሪ ወኪሎችን በሚወዳደሩባቸው የምርጫ ክልሎችና በስራቸው በሚገኙ የምርጫ ጣቢያዎች የማሰማራት ሕጋዊ መብት አላቸው፡፡ በዚህ መንገድ ዜጎች የፓርቲዎችና የግል ተወዳዳሪዎች ወኪሎች በመሆን ከመራጭነት በተጨማሪ ምርጫው የዴሞክራሲያዊ ምርጫ መስፈርቶችን ባሟላ መልኩ እንዲካሄድ በመከታተል ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማድረግ ይችላሉ፡፡

ዜጎች በዴሞክራሲያዊ ምርጫ ሂደት ውስጥ በተለያየ ደረጃ የምርጫ አስፈጻሚ በመሆን ይሳተፋሉ፡፡ በዚህ ከፍተኛ ኃላፊነት በሚጠይቅ ተግባር ላይ ለመሳተፍ በምርጫ ጣቢያ ወይም በምርጫ ክልል ደረጃ ዜጎች ይሳተፋሉ፡፡ እነዚህ ዜጎች ከመንግስታዊ ተቋማት ወይም መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ሊመለመሉ እንደሚችሉ የምርጫ ሕጉ ይደነግጋል፡፡ የምርጫ አስፈጻሚ ሆነው የሚመደቡ ሰዎች ገለልተኛ የሆኑና ከፖለቲካ ወገንተኝነት ነጻ የሆኑ የየትኛውም የምክር ቤት አባላት ያልሆኑ እንዲሆኑ የምርጫ ሕጉም ሆነ የምርጫ ቦርድ ደንብ ይደነግጋሉ፡፡

ስለሆነም በዚህ ኃላፊነት ላይ የሚሰማሩ ዜጎች ይህንን ተግባር በተሳካ ሁኔታ ለመተግበር እንዲችሉ በቂ ስልጠናና መረጃ እንዲኖራቸው ሊደረግ ይገባል።

### 5.3. በዴሞክራሲያዊ ምርጫ የሴቶች ተሳትፎ

የኢትዮጵያ ሕገ መንግስት ሴቶች በማናቸውም ሕገ መንግስቱ ባረጋገጣቸው መብቶችና ጥበቃዎች ከወንዶች ጋር እኩል መብት ያላቸው መሆኑን ይደነግጋል። በተጨማሪም ሴቶች በታሪካችንና በባህላችን የበታች ተደርገው ሲታዩ የቆዩ ስለሆነ በዚህ ምክንያት በፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መስኮች ከወንዶች ጋር ሲተያይ ወደኋላ ቀርተዋል። ይህንን ልዩነት ለማረም እንዲቻልና ሴቶች በፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መስኮች እንዲሁም በመንግስትና በግል ተቋማት ውስጥ ከወንዶች ጋር እኩል ተወዳዳሪና ተሳታፊ እንዲሆኑ ልዩ ትኩረትና ተጨማሪ የድጋፍ እርምጃ ተጠቃሚ የመሆን መብት እንዳላቸው ሕገ መንግስቱ በግልጽ አስፍሯል።

ስለዚህ የመንግስት ሕጎች፣ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ከላይ የተቀመጡትን ሕገ መንግስታዊ መርሆዎች መተግበር በሚያስችል መልክ የተቃኙ መሆን ይኖርባቸዋል። የመንግስት ሕጋዊ ማዕቀፎች የሴቶችን ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎ



ማሳደግ በሚያስችል መልክ መቀረጽ ይኖርባቸዋል። ለምሳሌ የፖለቲካ ፓርቲዎች ለመንግስት ኃላፊነት በታዎች እጩ ሲያቀርቡ ተገቢው የሴቶች ውክልና እንዲኖራቸው የሕግ ግፊትና ማበረታቻም ከመንግስት መደረግ ይኖርበታል። በዚህ ረገድ ፓርቲዎች ባቀረቡት የሴቶች እጩ ብዛት ላይ የተመሰረተ የምርጫ ወጪ መሸፈኛ ድጎማ ከመንግስት የሚያገኙበት አሰራር መዘርጋቱ በጎ እርምጃ ነው። የፖሊቲካ ፓርቲዎች በየደረጃው ያሉትን አመራሮቻቸውን ሲመርጡም የጾታ ውክልና እንዲኖራቸው የህግ ግፊትና ማበረታቻ ለማድረግ የሚያስችሉ ድንጋጌዎች በአዋጅ ቁ. 1162/2011 ውስጥ ተካቷል።

### 5.4. በዴሞክራሲያዊ ምርጫ የአካል ጉዳተኞች፣ የተፈናቃዮች፣አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ሰዎች ተሳትፎ

እነዚህ በርዕሱ የተመለከቱ የሕብረተሰብ ክፍሎች ከሌሎች የሕብረተሰብ ክፍሎች ተገቢውን የዴሞክራሲ ተሳትፎና ውክልና እንዲኖራቸው በተለየ ሁኔታ ትኩረት ያሻቸዋል። ስለሆነም የእነዚህ የሕብረተሰብ ክፍሎች ሁኔታ በተገቢው ተጠንቶ የመራጮች ትምህርት እንዲያገኙ፣ በመራጭነት/ተመራጭነት እንዲመዘገቡ እና እንዲመርጡ የሚያስችል እቅድ ወጥቶ መተግበር ይኖርበታል።

የአካል ጉዳተኞችን በተመለከተ ኢትዮጲያ ያፀደቀችው ዓለም ዓቀፍ የአካል ጉዳተኞች ኮንቬንሽን፤የአካል ጉዳተኞችም በፖለቲካው መስክ በነፃነት በሚመርጧቸው ተወካዮቻቸው አማካኝነት በመምረጥና በመመረጥ ከሌሎች ጋር ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግ እንደሚኖርባት ይደነግጋል።በዚህ ረገድ መንግስት የአካል ጉዳተኞች የምርጫ አሰራሮች፤ቁሶችናስፍራዎች ለአካል ጉዳተኞች ተስማሚ እንዲሆኑ ማድረግ በምርጫ ወቅት ድምጻቸውን በነፃነት እና በሚስጥር የሚሰጡበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤በምርጫ ወቅት እርዳታ የሚሹ የአካል ጉዳተኞች በሚመርጡት ሰው የመታገዝ መብት እንዲኖራቸው ማድረግ፤ተመርጠው በማናቸውም ደረጃ የማገልገል ዕድል እንዲኖራቸው ማድረግ፤አስፈላጊ የሆኑ የቴክኖሎጂ ድጋፍ ማድረግ እና በአጠቃላይ የአካል ጉዳተኞች ያለ አድልዎ ከሌሎች ጋር በእኩልነት በፖለቲካና እና በሕዝብ አስተዳደር ጉዳዮች እንዲሳተፉ ማድረግና ማበረታታት ያለበት መሆኑ በኮንቬንሽኑ አንቀፅ 29 ሥር ተደንግጓል።

የምርጫ አዋጅ ቁ. 1162/2011 ከላይ የተገለፁት በምርጫ ወቅት የኮንቬንሽኑ አንኳር ድንጋጌዎች ተፈፃሚ የሚሆኑበትን ሥርዓት ዘርግቷል ለማለት ይቻላል፡፡አዋጁ የአካል ጉዳተኞች የጉዳት ዓይነት በመራጮች መዝገብ ላይ እንዲገለፅ ከማድረግ አንስቶ ለዕጩነት ለመቅረብ የሚያስፈልገው የድጋፍ ፊርማ ብዛት ከሌሎች ዕጩዎች ያነሰ እንዲሆን፡፡እንዲሁም የአካል ጉዳተኞች በፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ የሚያደርጉት ተሳትፎ ከፍ እንዲል እነርሱን በአባልነት በዕጩነት እና በአመራርነት ለሚያሳትፉ የፖለቲካ ፓርቲዎች ተጨማሪ የገንዘብ ድጋፍ የሚያደርግበት የማበረታቻ ሥርዓት ዘርግቷል፡፡

አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ብሄረሰቦችንና ሕዝቦችን በተመለከተ የኢትዮጲያ ሕገ መንግስት በሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ውስጥ ውክልና እንዲኖራቸው አድርጓል፡፡ይህም የእነዚህን የሕብረተሰብ ክፍሎች በፌዴራል የሕግ አውጪው አካል ውስጥ ውክልና እንዲያገኙ አስችሏቸዋል፡፡

## ምዕራፍ 6. በምርጫ ሒደት የሚነሣ አቤቱታ እና ክርክር የሚፈታበት ተቋም እና የሚስተናገዱበት ሥርዓት፤

ሰልጣኞች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፤

- ከመራጮች ምዝገባ ጀምሮ እስከ ውጤት አገላለጽ ድረስ በተለያየ ምክንያት በተወዳዳሪ ፓርቲዎችና እጩዎች የሚነሱ ቅሬታዎች የሚፈቱበትን አግባብ ይገልጻሉ፤
- በተለያየ ምክንያት በተወዳዳሪ ፓርቲዎችና እጩዎች የሚነሱ ቅሬታዎች አፈታት ላይ ዜጎች ስለሚኖራቸው ሚና ያብራራሉ፤

### ተግባር 6፡- የቡድን ውይይት

**አሰልጣኝ፡-** ተሳታፊዎችን በአምስት በአምስት በማድረግ ቡድኖችን ያዋቅሩ። ከዚያም የሚከተሉትን ጥያቄዎች ያቅርቡላቸውና ውይይት በማድረግ የመፍትሄ ሃሳቦች ጥቆማ እንዲያደርጉ ይጠይቁ።

- ✓ ከመራጮች ምዝገባ ጀምሮ፣ በእጩዎች ምዝገባ ወቅት፣ በድምጽ አሰጣጥ ሂደት፣ በድምጽ ቆጠራ ሂደት፣ በውጤት አገላለጽና የምርጫ ውጤት ላይ በተለያየ ምክንያት በተወዳዳሪ ፓርቲዎችና እጩዎች ቅሬታዎች ቢነሱ በምን ሁኔታ ይፈታሉ?
- ✓ ቅሬታዎች አፈታት ላይ ዜጎች የሚኖራቸው ሚና ምን መሆን አለበት?

**አሰልጣኝ፡-** እያንዳንዱ ቡድን የተወያየባቸውን የማጠቃለያ ነጥቦች በየተወካዮቻቸው በማቅረብ ተሳታፊዎች አጠቃላይ ውይይት ያካሂዱ። በመጨረሻም የሚከተለው ጽሁፍ ላይ ያሉ ሃሳቦችን በማንጸባረቅ ውይይቱን ይደምድሙ።

ከመራጮች ምዝገባ ጀምሮ በተለያየ ምክንያት በተወዳዳሪ ፓርቲዎችና እጩዎች ቅሬታዎች ሊነሱ ይችላሉ። ለምሳሌ በምርጫ ቅስቀሳ ወቅት በሚደረጉ ንግግሮች ምክንያት በፓርቲዎች እና በደጋፊዎች መካከል ቅሬታና አለመግባባት ሊከሰት ይችላል። አንዳንድ ደጋፊዎች የሌሎች ፓርቲዎችን እጩዎች ምልክቶችንና ፖስተሮችን የሚያበላሹበት ወቅትም አለ። በሌላ በኩል ደግሞ ለተወዳዳሪ የፖለቲካ ፓርቲዎቹ በሕግ የተፈቀዱ መብቶች በአጠቃላይ ቅሬታዎች ከመራጮች ምዝገባ ጀምሮ፣ በእጩዎች ምዝገባ ወቅት፣ በድምጽ አሰጣጥ ሂደት፣ በድምጽ ቆጠራ ሂደት፣ በውጤት አገላለጽና የምርጫ ውጤት ላይ ሊከሰቱ ይችላሉ። እነዚህ ቅሬታዎች አይቀሬ ናቸው። ስለሆነም ቅሬታዎቹ የሚፈቱበት ስርዓትና ተቋም ያስፈልጋል ማለት ነው። የኢትዮጵያ የምርጫ ሕግ ቅሬታ የሚስተናገድበትን ስርዓትና ቅሬታዎቹ የሚፈቱባቸውን ተቋማት አመልክቷል። ቀጥለው ቀርበዋል።

### 6.1. በምርጫ ወቅት የሚከሰቱ ቅሬታዎች እና አለመግባባቶች

የኢትዮጵያ የምርጫ ሕግ ከመራጮች ምዝገባ ሂደት ጀምሮ እስከ የምርጫ ውጤት ገለጻ ወይም ውሳኔ ድረስ የሚነሱ ቅሬታዎችና አቤቱታዎች እንዴትና በማን እንደሚፈቱ በ አዋጅ ቁ. 1162/2011 ደንግጓል። የምርጫ ሕጉ በሚቀርቡ ቅሬታዎች ላይ አስተዳደራዊ የሆነ ውሳኔ የሚሰጡ መድረኮችንና እነዚህ አስተዳደራዊ መድረኮች የሚሰጧቸው ውሳኔዎች ደግሞ በውሳኔዎቹ ቅር በተሰኙ ወገኖች በይግባኝ መለክ ለመደበኛ ፍ/ቤቶች ቀርበው የሚታዩበትን ስርዓት ተዘርግቷል። አስተዳደራዊ የሆኑት የቅሬታ መፍቻ መድረኮቹ ከምርጫ ጣቢያ ጀምሮ እንደ ሁኔታው እስከ ምረጫ ቦርድ ድረስ ያለው ሲሆን በፍ/ቤቶችም ደረጃ ከወረዳ ፍ/ቤት ጀምሮ እስከ ፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ድረስ ባለጉዳዮች የሚስተናገዱበትን ስርዓት በሕጉ ተዘርግቷል።

የምርጫ ሕጉ ከላይ ከተገለጹት የምርጫ ቅሬታ መወሰኛ መድረኮች በተጨማሪ የሚነሱ ቅሬታዎችንና አለመግባባቶችን በውይይትና በስምምነት ለመፍታት ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ የፖለቲካ ድርጅቶች የጋራ መድረክ በየደረጃው እንደሚያቋቁም ይደነግጋል።

እነዚህ ከላይ የተመለከቱት ተቋማትና እንዲሁም ባለጉዳይ ሊሆኑባቸው የሚችሉት የምርጫ ተሳታፊዎች ሊተገብሯቸው የሚገቡ መርሆዎችን የምርጫ ሕጉ ደንግጓል። በዚሁ መሰረት፤

1) ክርክሮች ወይም አቤቱታዎች የቀረቡለት ውሳኔ ሰጭ አካል የምርጫው ሂደት ነፃ፣ ፍትሀዊና ሰላማዊ ሆኖ እንዲቀጥል ለማስቻል የምርጫውን የጊዜ ሰሌዳ መሰረት በማድረግ መቀበልና አፋጣኝ ውሳኔ መስጠት አለበት።

2) ማንኛውም አቤቱታም ሆነ በማንኛውም አቤቱታ ውሳኔ በፅሁፍ የሰፈረ መሆን አለበት።

3) አቤቱታ ሰሚ አካላት የሚቀርብላቸው አቤቱታ የደረሳቸው መሆኑን የሚያሳይና አቤቱታው የቀረበበትን ቀንና ሰዓት የሚገልፅ ማስረጃ ሊሰጡ ይገባል።

4. ቦርዱ ለሚቀርቡለት አቤቱታዎች በወቅቱ መፍትሔ ለመስጠት የሚያስችለው አሰራር በየደረጃው በሚገኙ የምርጫ ፅህፈት ቤቶች ይዘረጋል።

5) ቦርዱ በምርጫ ሒደት በሚቀርቡለት አቤቱታዎች ላይ ውሳኔ ለመስጠት የሚያግዙ የፍሬ ነገር የማስረጃ እና የሕግ ጉዳዮች አጣርቶ የውሳኔ ሐሳብ የሚያቀርብለት  አግባብነት ካላቸው የሞያ ዘርፎች የተውጣጡ ባለሞያዎችን የያዘ አጣሪ ጉባኤ ሊያቋቁም ይችላል።

6) ቦርዱ ወይም በየደረጃው የሚገኙ የምርጫ አስፈፃሚዎች የቀረቡ አቤቱታዎችን ለመፍታት የሚያስፈልገውን መረጃ እን ዲቀርቡ ማንኛውም የሚመለከተውን ሰው ወይም የመንግስት ድርጅት መጥራት እና የሚፈለገውን ጉዳይ በአካል ቀርቦ እንዲያስረዳ ወይም እንዲያቀርብ ሊያዝ ይችላል።

7) ቦርዱ የምርጫ ሂደትን የሚያደናቅፍ ማናቸውም ወንጀል መፈፀሙን ወይም በመፈፀም ላይ መሆኑን ሲያውቅ ወይም በመረጃ የተደገፈ አቤቱታ ሲደርሰው ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ጉዳዩን ወደሚመለከተው አካል ይመራል፣ ይከታተላል።

8) በዐዋጁ በተቀመጠው ጊዜ አቤቱታውን ያላቀረበ ማንኛውም ሰው አቤቱታ የማቅረብ መብቱ በይርጋ ይታገዳል።

9) በእያንዳንዱ ክልል እና በፌዴራል ባሉ ፍርድ ቤቶች የምርጫ ጉዳይ ችሎቶች የመራጮች ምዝገባ ከመጀመሩ አንድ ወር ቀደም ብሎ እንደአስፈላጊነቱ ያደራጃሉ።

10) ቦርዱ አግባብነት ካለው የፌዴራል ወይም የክልል የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ጋራ በመመካከር ከላይ በተገለፀው መሰረት የምርጫ ችሎቶች እንዲደራጁ እና በቂ ዳኞች እንዲኖራቸው ያደርጋል።

11) ቦርዱ ከፌዴራል እና ከክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች ጋር በመተባበር ከላይ በተገለፁት የምርጫ ችሎቶች ላይ የሚመደቡ ዳኞች በቂ ስልጠና እንዲያገኙ ያደርጋል።

### 6.2. በምርጫ ሂደት የሚከሰቱ ቅሬታዎች እና አቤቱታዎች መፍቻ ሥርዓት እና ተቋማት

የኢትዮጵያ የምርጫ ሕግ ከመራጮች ምዝገባ ሂደት ጀምሮ እስከ የምርጫ ውጤት ገለጻ ወይም ውሳኔ ድረስ የሚነሱ ቅሬታዎችና አቤቱታዎች እንዴትና በማን እንደሚፈቱ ደንግጓል። የምርጫ ሕጉ በሚቀርቡ ቅሬታዎች ላይ አስተዳደራዊ የሆነ ውሳኔ የሚሰጡ መድረኮችንና እነዚህ አስተዳደራዊ መድረኮች የሚሰጧቸው ውሳኔዎች ደግሞ በውሳኔዎቹ ቅር በተሰኙ ወገኖች በይግባኝ መልክ ለመደበኛ ፍ/ቤቶች ቀርበው የሚታዩበትን ስርዓት ተዘርግቷል።

አስተዳደራዊ የሆኑት የቅሬታ መፍቻ መድረኮቹ ከምርጫ ጣቢያ ጀምሮ እንደ ሁኔታው እስከ ምረጫ ቦርድ ድረስ ያለው ሲሆን በፍ/ቤቶችም ደረጃ ከወረዳ ፍ/ቤት ጀምሮ እስከ ፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ድረስ ባለጉዳዮች የሚስተናገዱበትን ስርዓት በሕጉ ተዘርግቷል። የምርጫ ሕጉ ከላይ ከተገለጹት የምርጫ ቅሬታ መወሰኛ መድረኮች በተጨማሪ የሚነሱ ቅሬታዎችንና አለመግባባቶችን በውይይትና በስምምነት ለመፍታት ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ የፖለቲካ ድርጅቶች የጋራ መድረክ በየደረጃው እንደሚያቋቁም ይደነግጋል።

### 6.2.1. በመራጮች ምዝገባ ሂደት ስለሚነሱ ክርክሮች

በመራጮች ምዝገባ ሂደት የሚነሱ ክርክሮችን አፈታት በተመለከተ የምርጫ ሕጉ የሚከተለውን ይደነግጋል።

1) ማንኛውም ሰው በመራጭነት ከመመዝገብ የተከለከለ እንደሆነ ለምርጫ ጣቢያው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ አቤቱታውን አቅርቦ ውሳኔ የማግኘት መብት አለው።
2) "መብት የሌለው ወይም በመራጭነት መመዝገብ የሌለበት ሰው ያለአግባብ ተመዝግቧል" የሚል ተቃውሞ ያለው ሰው ወይም የፖለቲካ ድርጅት ተቃውሞውን ለምርጫ ጣቢያው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ አቅርቦ ውሳኔ የማግኘት መብት አለው።
3) ከላይ በተራ ቁ. 1 እና 2 መሠረት፤ አቤቱታ የማቅረቡያ ጊዜ ከመራጮች የምዝገባ ቀን ጀምሮ የመራጮች መዝገብ ለሕዝብ ይፋ የሚሆንበት ጊዜ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ይሆናል።
4) የምርጫ ጣቢያው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የቀረበለትን አቤቱታ መርምሮ በ 5ት ቀናት ውስጥ ውሳኔውን በፅሑፍ ይሰጣል።
5) ከላይ በተራ ቁ. 1 እና 2 ለቀረበው አቤቱታ የምርጫ ጣቢያው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በ 5ት ቀናት ውስጥ ውሳኔ ካልሰጠ አቤቱታ አቅራቢው ለምርጫ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ በ 5ት ቀናት ውስጥ አቤቱታ በማቅረብ ውሳኔ የማግኘት መብት አለው።
6) በምርጫ ጣቢያው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ለምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የሚቀርብ አቤቱታ ውሳኔ ከተሰጠበት በ 5ት ቀናት ውስጥ መቅረብ ይኖርበታል።
7) የምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የቀረበለትን ይግባኝ መርምሮ በ 5ት ቀናት ውስጥ ውሳኔውን በጽሁፍ ይሰጣል።
8) የምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በ 5ት ቀናት ውስጥ ውሳኔ ካልሰጠ ወይም ቅሬታ አቅራቢው በተሰጠው ውሳኔ ያልተስማማ እንደሆነ በ 5ት ቀናት ውስጥ ስልጣን ላለው በየደረጃው ላሉ የፌዴራል ወይም የክልል ፍ/ቤት ጉዳዩ እንዲታይለት አቤቱታ የማቅረብ መብት አው።አቤቱታ የቀረበለት ፍ/ቤትም የቀረበለት አቤቱታ ለመወሰን የሚያስፈልጉ ማስረጃዎችን አስቀርቦ በመመርመር ውሳኔ ይሰጣል።
9) የምርጫ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ በሚሰጠው ውሳኔ መሰረት የምርጫ ጣቢያው ፅህፈት ቤት ስራውን ያከናውናል።

### 6.2.2. በዕጩዎች ምዝገባ ሂደት ስለሚነሱ ክርክሮች

1) ማንኛውም ሰው ወይም የፖለቲካ ድርጅት በእጩነት ከመመዝገብ የሚያግድ ሁኔታ ሲያጋጥመው ለምርጫ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ቅሬታውን አቅርቦ መልስ የማግኘት መብት አለው።

2) አንድ በዕጩነት የተመዘገበ ሰው በዕጩነት መቅረብ የለበትም የሚል ተቃውሞ ያለው ሰው ወይም የፖለቲካ ድርጅት ለምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አቤቱታውን አቅርቦ ውሳኔ የማግኘት መብት አለው፡

3) ከላይ በተራ ቁ. 1 እና 2 መሠረት የሚቀርብ አቤቱታ የማቅረቢያ ጊዜ ከዕጩዎች የምዝገባ ቀን ጀምሮ የተመዘገቡ ዕጩዎችይፋ እስከሚሆንበት ቀን ድረስ ይሆናል፡፡

4) የምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የቀረበለትን አቤቱታ በ5ት ቀናት ውስጥ ውሳኔን በፅሑፍ ይሰጣል፡፡

5) ከላይ በተራ ቁ. 4 መሠረት በምርጫ ክልል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በተሰጠ ውሳኔ ቅር የተሰኘ የፖለቲካ ድርጅት ዕጩ ወይም የግል ዕጩ ፤ በቅርንጫፍ ፅ/ቤት ለሚቋቋም ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በ7 ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፡፡

6) የክልሉ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ቅሬታ በፅሕፈት ቤቱ ኃላፊ ሰብሳቢነት የሚመራ ሆኖ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት የሚሰየሙ ሁለት ተጨማሪ አባላት ይኖሩታል፡፡

7) የክልሉ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በ7ት ቀናት ውስጥ ውሳኔ ካልሰጠ ወይም ቅሬታ አቅራቢው በተሰጠው ውሳኔ ካልተስማማ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቤቱታ የማቅረብ መብት አለው፡ ችሎቱም የቀረበለትን አቤቱታ ለመወሰን የሚያስፈልጉ ማስረጃዎችን አስቀርቦ በመመርመር በ15 ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

8) የክልሉ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በሚሰጠው ውሳኔ መሠረት የምርጫ ክልሉ ስራውን ያከናውናል፡፡

### 6.2.3. በድምፅ አሰጣጥ ሂደት ስለሚነሱ ክርክሮች



በድምፅ አሰጣጥ ሒደት የሚነሱ ክርክሮችን አፈታት በተመለከተ ዐዋጅ ቁ.1162/2011 አንቀፅ 154 የሚከተለውን ይደነግጋል፡፡

1) አንድ የተመዘገበ መራጭ ድምፅ ከመስጠት የሚያግደው ሁኔታ ሲፈጠር ቅሬታውን ወዲያውኑ ለምርጫ ጣቢያ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ በማቅረብ ውሳኔ የማግኘት መብት አለው፡፡

2) የምርጫ ጣቢያ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴም፡-

ሀ) ጉዳዩን በማጣራት መራጩ ድምፁን እንዲሰጥ ሊወስን ይችላል፤ ወይም

ለ) ጊዜያዊ ድምፅ እንዲሰጥ በማድረግ ጉዳዩን ወደ ምርጫ ክልሉ ፅሕፈት ቤት በመላክ ውሳኔ እንዲያገኝ ሊያደርግ ይችላል፡፡

I. ከላይ በተራ ቁ. 2(ለ) መሰረት ጊዜያዊ ድምፅ የሰጠ መራጭ ከምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ወይም እንደሁኔታው ሥልጣን ካለው የፌዴራል ወይም የክልል ፍ/ቤት የመምረጥ መብት እንዳለው የሚገልፅ ውሳኔ የድምፅ ማዳመሩ ከመጠናቀቁ በፊት ለምርጫ ክልሉ ጽህፈት ቤት ካላቀረበ የሰጠው ጊዜያዊ ድምፅ ውድቅ ይደረጋል።

II. በምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ውሳኔ ቅር የተሰኘ በተራ ቁ. 2(ለ) በተመለከተው መሠረት ጊዜያዊ ድምፅ ማቅረብ ይችላል።

III. የአንድን መራጭ ድምፅ መስጠት የሚቃወም ሰው ከላይ በተደነገገው መሠረት አቤቱታውን በየደረጃው የማቅረብ እና ውሳኔ የማግኘት መብት አለው።

### 6.2.4. በቆጠራ ሂደትና ውጤት ስለሚነሱ ክርክሮች

በድምፅ ቆጠራ ሂደት እና በውጤቱ ላይ የሚነሱ ክርክሮችን አፈታት በተመለከተ፤ አዋጅ ቁ. 1162/2011 የሚከተለውን ይደነግጋል።

1) በድምፅ ቆጠራ ሂደትና በውጤቱ ላይ ቅሬታ ያለው ማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት ወይም የግል እጩ ወይም ወኪል ቅሬታውን ለምርጫ ጣቢያው አቤቱታ ሰሚ ወዲያውኑ በማቅረብ ሊያስወስን ይችላል። በኮሚቴው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን አቤቱታውን በ2ት ቀናት ውስጥ ለምርጫ ክልል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ሊያቀርብ ይችላል።
2) የምርጫ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ከላይ በተ.ቁ. 1 መሰረት የቀረበለትን አቤቱታ መርምሮ  በሁለት ቀናት ውስጥ ውሳኔ በፅሑፍ ይሰጣል።
3) ከላይ በተ.ቁ. 2 መሰረት በተሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ አቤቱታ አቅራቢ ውሳኔ በተሰጠው በአምስት ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለቦርዱ ማቅረብ ይችላል። ቦርዱ የቀረበውን ቅሬታ መርምሮ መርምሮ በ10 ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል።
4) ከላይ በተ.ቁ. 3 መሠረት በቦርዱ በተሠጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ አቤቱታ አቅራቢ ውሳኔ በተሰጠው በ10 ቀናት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አቤቱታ ማቅረብ ይችላል።ፍ/ቤቱም የቀረበለትን ቅሬታ ለመወሰን የሚያስፈልጉ ማስረጃዎችን አስቀርቦ በመመርመር ውሳኔ ይሰጣል።
5) የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤትም ከላይ በተ.ቁ. 4 መሠረት ለቀረበለት አቤቱታ ከአንድ ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል።
6) ከላይ በተጠቀሱት ተራ ቁጥሮች መሠረት በድምፅ ቆጠራ ሒደት እና በውጤቱ ላይ የቀረበ ቅሬታ ወይም ይግባኝ በሚታይበት ጊዜ እንደአግባብነቱ የምርጫ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ቦርዱ ወይም የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት፤ቅሬታ የቀረበበት የምርጫ ክልል ውጤት እንዳይገለፅ ሊያዝ ይችላል።

Initiative Africa

Tel: +251 116 62 26 40/ 41
Fax: +251 116 62 26 42
Email: info@initiaitveafrica.net
web: www.initiaitveaftica.net

© ኢኒሽየቲቭ አፍሪካ
2013 ዓ.ም